## ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ፤

አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣

በ

ቆንጂት ሾደኖ

ሚያዚያ፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ፤

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣

በ

ቆንጂት ሸደኖ

ዋና አማካሪ፡- ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡- ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)

ሚያዚያ፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

## ጅማ ዩኒቨርሰቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች)ና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

## የአማካሪ ይሁንታ

ተማሪ ቆንጂት ሾደኖ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል በድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት "አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ" በሚል ርዕስ የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሑፏን ከአማካሪዎቿ የተሰጠውን አስተያየት ተቀብላ በማስተካከል ስትሠራ የቆየች ሲሆን ጥናታዊ ጽሑፉ ለተቋሙ መቅረብ የሚችል መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

የአማካሪ ስም፡- -------------------- ፊርማ፡- ------------------- ቀን፡- ----------------

"አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በቆንጂት ሾደኖ የቀረበው ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈተና ቦርድ አባላት ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈተና ቦርድ አባላት፤

ዋና አማካሪ ..........................................ፊርማ.........................ቀን..................

የውጭ ፈታኝ.............................................ፊርማ.........................ቀን.......................

የውስጥ ፈታኝ ...........................................ፊርማ.........................ቀን.......................

## ማውጫ


ይዘት ገጽ

ምስጋና ..... viii

አጠቃሎ ..... ix

1.1. የጥናቱ ዳራ ..... - 1 -

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... - 6 -

1.3. የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ..... - 7 -

1.4. የጥናቱ ዋና ዓላማ ..... - 7 -

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... - 8 -

1.6. የጥናቱ ወሰን ..... - 8 -

2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ዳሰሳ ..... - 9 -

2.1.1. የአንብቦ መረዳት ምንነት ..... - 9 -

2.1.2. የመርሃ ትምህርት ምንነት ..... - 12 -

2.1.3. የመርሃ ትምህርት አስፈላጊነት ..... - 12 -

2.1.4. የመርሃ ትምህርት ጥቅም ..... - 14 -

2.1.5. የመርሃ ትምህርት ዓላማዎች ..... - 15 -

2.1.6. የመርሃ ትምህርት አለባውያን (Elements of Syllabus) ..... - 15 -

2.1.7. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነትና ባህሪ ..... - 18 -

2.1.8. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አደረጃጀት ..... - 21 -

2.1.9. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀት ..... - 21 -

2.1.10. የአንብቦ መረዳት ችሎታን መለካት ..... - 23 -

2.1.11. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ ..... - 24 -

2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ..... - 25 -

ምዕራፍ ሦስት፤ የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ..... - 27 -

3.1. የጥናቱ ንድፍ ..... - 27 -

3.2. የጥናቱ መረጃ ምንጮች ..... - 27 -

3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ..... - 27 -

3.3.1. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ዘዴ ..... - 27 -

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ..... - 28 -

3.4.1. የሰነድ ፍተሻ - 28 -
3.4.2. ቃለ መጠይቅ - 28 -
3.5. የመረጃ አደረጃጀት - 29 -
3.6. የመረጃ አተናተን ዘዴ - 29 -
ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ - 30 -
4.1. የመረጃ ትንተና - 30 -
4.1.1. ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ ትንተና - 30 -
4.1.2. በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና - 33 -
4.1.3. በቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና - 40 -
4.2. የውጤት ማብራሪያ - 47 -
ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያና አስተያየት - 50 -
5.1. ማጠቃለያ - 50 -
5.2. አስተያየት - 51 -
አባሪዎች - 58 -

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1፡ በአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የሚገኙባቸው ገጾችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ............................................- 32 -

ሰንጠረዥ 2፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አጠቃላይ መግለጫ.......................................................................................................- 33 -

ሰንጠረዥ 3፡ በአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር በቀረቡ መልመጃ ጥያቄዎች ዝርዝር መግለጫ..........................................- 36 -

ሰንጠረዥ 4፡- ለሰነድ ፍተሻው የተዘጋጁ መለኪያዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ስላላቸው ተጣጥሞሽ የሚያሳይ መረጃ...........................................................................................- 38 -

ሰንጠረዥ 5፡- ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን ዳራዊ መረጃ .............................- 40 -

ሰንጠረዥ 6፡- ለክፍል አንድ ቃለ መጠይቅ መምህራን የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ መረጃ..- 41 -

ሰንጠረዥ 7፡- ከክፍል ሁለት ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ............................................- 45 -

# ምስጋና

ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ መሳካት በነገር ሁሉ ለረዳኝ እግዚአብሔር በቅድሚያ ክብር ምስጋና ይሁን፡፡ በመቀጠል ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ስህተቴን በማረምና ገንቢ አስተያየት በመስጠት ከርዕስ መረጣው እስከ ጥናቱ መጠናቀቅ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለዋና አማካሪዬ ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር) እና ለረዳት አማካሪዬ ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር) ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለው፡፡ ጥናቴ ከግብ እንዲደርስ ተገቢ መረጃ ለሰጡኝ በቴፒ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስረኛ ክፍል ተማሪዎችን አማርኛ ቋንቋ እያስተማሩ ላሉ መምህራን ከልብ የመነጨ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ፡፡ በመጨረሻም ይህ ጥናት የተሳካ እንዲሆን በሀሳብ ከጎኔ ለሆኑልኝ ጓደኞቼና ቤተሰቦቼ ምስጋና አለኝ፡፡

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት ዋና ትኩረቱ አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡ ለጥናቱ ስኬት ተገቢ መረጃ እንዲሰጡ የተመረጡት በ 2016 ዓ.ም በቴፒ ከተማ አስተዳደር፣ በቴፒ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ አስረኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራን ናቸው፡፡ ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት የዋሉት በ2014 ዓ.ም በአዲስ መልክ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ እንደ ፌደራል መማሪያ መጽሐፍ፣ በ2014 ዓ.ም በአዲስ መልክ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ እንደ ፌደራል የመምህር መምሪያ መጽሐፍ እና በ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በቴፒ ከተማ አስተዳደር በቴፒ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን እያስተማሩ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ ጥናቱ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍ የተከተለ ሲሆን መረጃው በመጠናዊ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ ለጥናቱ የዋሉ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ ክፍሉን እያስተማሩ ካሉ መምህራን በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጠው ተሰብስቧል፡፡ በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ተገቢ የትምህርት ገለጻ ከተደረገ በኋላ መሆኑን ውጤቱ አሳይቷል፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ ግቦችን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውንና በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ሁሉንም የመልመጃ ዓይነት አካትተው የያዙ መሆናቸውን በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ አመለካቷል፡፡ በተገኘው መረጃ መማሪያ መጽሐፉና መርሀ ትምህርቱ ተጣጥሞሽ ያላቸው መሆኑ ተፈትሾ ተረጋግጧል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ትምህርትና ልማት በቅርበት የተያያዙ፣ ግባቸው አንድ የሆነ ጥረቶች ናቸው:: ትምህርት የልማትና ማህበራዊ ለውጥ ቁልፍ መሳሪያ ነው የሚባለበት ዋናው ምክንያትም ይህ ነው:: አሁን የምንኖርበት ፈጣን እና ተለዋዋጭ ዓለም በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ አዲስ እውቀት፣ ችሎታና አመለካከት ይፈልጋል:: ከዚህ አላማ አንጻር ሥርዓተ ትምህርቱ ብሉ ፕሪንት ብቻ ሳይሆን የአንድ ሀገር የትምህርት ስርዓት ነጸብራቅ ሆኖ ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጥ መሆን አለበት::

ኢትዮጵያ አዲስ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ከጀመረችና ተግባራዊ ካደረገች ወደ ሶስት አስርት አመታት ተቆጥሯል:: ከ1994ቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጀምሮ አገራችን በተደራሽነት፣ በፍትሃዊነትና በአግባብነት አመርቂ እድገት አስመዝግባለች:: የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ጠንካራ ጥረቶች ተደርገዋል፤ አሁንም እየተደረጉ ናቸው:: ይህንን እድገት ለማስቀጠል የትምህርት ሚኒስቴር በ2021 አዲስ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርአተ ትምህርት ማዕቀፍ አዘጋጅቷል:: ማዕቀፉ ሁሉንም የቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶችን ያጠቃልላል:: ማዕቀፉ በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ውስጥ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ መርሆችን ለማጠናከር ያለመ ሲሆን፣ በቀጣይ የሥርዓተ ትምህርት ቁሳቁሶች ዝግጅት ላይ መመሪያ ይሰጣል:: ይህን የመምህሩ መመሪያና የተማሪ መማሪያ መጽሐፍን ጨምሮ፤ በንቃት የመማር ዘዴዎች የማስተማሪያ ብልሃቶች ላይ የተመሰረተ ነው::

ለዚህ አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት እ.ኤ.አ. በ2018 የተካሄዱት የትምህርት ፍኖተ ካርታ ጥናቶችና ምክሮች እንደ ዋና መነሻ ያገለግላሉ:: የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ቁሳቁሶች ይዘቱን ከተማሪዎች ዕድሜ ጋር በማመጣጠን፣ አገር በቀል ዕውቀትን መጠቀምን፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቴክኖሎጂን ለመማር እና ለማስተማር መገልገልን፣ የሙያ ይዘቶችን በማዋሃድ፣ የሞራል ትምህርትን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት በማካተት የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርትን በደረጃው እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያስችልና የተማሪዎች የተለያዩ ፍላጎቶች ግምት ውስጥ ያስገቡ የትምህርት ዓይነቶችን ለማካተት ጥረት ተደረጓል::

በየትኛውም ሀገር የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል አዲስ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ የመማሪያ መጽሃፍትን ማሳተምና የመምህራን መመሪያዎች መታተም በምንም መልኩ ብቸኛ መፍትሄ አይደሉም። ቀጣይነት ላለው መሻሻል የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ጥረት ይጠይቃል። በመሆኑም የአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ካለይ የተገለጹ መሠረታዊ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ በ2014 ዓ.ም በአዲስ መርሀ ትምህርት መነሻ በአዲስ መልክ የተዘጋጀ መሆኑን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር (2014) አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በመቅድም ክፍል ያብራራል።

የዚህ ጥናት ትኩረት አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ ሲሆን በጥናቱ አዲሱ መማሪያ መጽሐፍ ቀደም ሲል ሲተገበር ከቆየው መማሪያ መጽሐፍ ምን ያህል የተሻለ እንደሆነ ተዳስሷል።

ስለቋንቋ ክሂል ሲነሳ ማንበብ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ ክሂል እንደሆነ ይታመናል። የቋንቋ ክሂሎች የመልዕክት መቀበያ እና የመልዕክት ማስተላለፊያ ተብለው በሁለት መልክ የሚታዩ ሲሆን ማንበብ መልዕክትን ከምንቀበልበት ክሂሎች አንዱ ነው። ማንበብን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ሀሳብ ሰንዝረዋል። ስለሆነም የምሁራንን ሀሳብ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

እንደ Grellet (1981፡8) አገላለጽ ማንበብ ማለት መገመት፣ መተንበይ፣ ማመሳከር እና የራስን ጥያቄ መጠየቅን የሚያጠቃልል ንቁ ተሳትፎ የሚያስፈልገው ሂደት ነው። David (2005፡1) በበኩላቸው ማንበብ ጸሐፊው በስራው ያሰፈረውን ቁም ነገር ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነው። አንባቢው በንባብ ሂደት የጽሁፉን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት፤ መረጃን ከውስጥ ለይቶ ለማውጣት፤ የጸሐፊውን (የደራሲውን) ሀሳብ ይመረምራል በማለት ይገልጻሉ።

ምሁራኑ እንደገለጹት ማንበብ ማለት መገመት፣መተንበይ፣ የአእምሮን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ እና ፀሀፊው ያሰፈረውን ቁም ነገር መረዳትን የሚጠይቅ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

Hittleman (1998፡7) "ማንበብ ድምፅን ከመለየት አንስቶ ትርጉም እስከ ማዋቀር ድረስ በመዝለቅ ቃላት የተሸከሙትን ሀሳብ፣ ስሜት እውቀትና ራእይ ማስተዋል ውስብስብ አእምሯዊ ሂደት ነው" ሲሉ Carrell (2oo6፡12) በበኩላቸው "ማንበብ ውስብስብ አእምሯዊ ሂደት የሚንጸባረቅበት፣ በጸሀፊ የቀረበን ጽሁፍ ሀሳብ (ስሜት) ለመለየት፣ለመገንዘብ (ለመረዳት) ፣

ለመተርጎምና ለመተንተን አካላዊ፣አእምሯዊእና ስሜታዊ ጉዳዮችን ያካተተ መስተጋብራዊ ሂደት ነው" ብለውታል፡፡

ከላይ ብያኔ ከሰጡት ምሁራን ዘንድ የሚንጸባረቀው ማንበብ ዘላቂነት ያለው በጸሀፊው የቀረበውን ጽሁፍ ማስተዋል፣መተርጎም፣መተንተን የሚጠይቅ ውስብስብ የሆነና አካላዊ፣ አእምሯዊና ስሜታዊ ጉዳዮች ያካተተ መሆኑን ነው፡፡

የማንበብ ትምህርት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በፅሁፍ ውስጥ የቀረቡ አዳዲስ መረጃዎችን በቀላሉና በአጭር ጊዜ ሀሳባቸውን መገንዘብ መቻል ነው፡፡እንዲሁም አንብቦ መረዳት አእምሯዊ ሂደቶችን በማለፍ የሚዳብር ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ አንብቦ መረዳት በፅሁፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የመገንዘብ ወይም የመረዳት እንደሆነና የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባል (Ur፡ 1996)፡፡ Nuttal (1996)ና Shanehan (2006) እንዳብራሩት አንብቦ መረዳት የአንድን ፅሁፍ ሀሳብ አእምሯዊ እውቀትና ስነልሳናዊ ችሎታ በማጣመር ለፅሁፉ ትርጉም መስጠት፣አውዳዊና ከዐውድ ውጭ የሆኑ ፍችዎችን መገንዘብን ያጠቃልላል፡፡ አንብቦ መረዳት አእምሯዊ ክዋኔ ብቻ ሳይሆን ስሜታዊ ተግባር ጭምር ነው፡፡ ስለዘህ አንብቦ መረዳት የጽሁፉ መልክት መረዳት፣ አውዳዊና ከአውድ ውጭ የሆነ ፍችን መገንዘብን እና አእምሯዊና ስሜታዊ ተግባር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታ በትምህርት ቤት ብቻ ሳይገደብ በተማሪዎች የህይወት ዘመን የሚኖረው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የማንበብ ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚያዳብር መሆን ተማሪዎችን ዘለቄታዊ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል፡፡ የቋንቋ ትምህርት ብሎም የአንብቦ መረዳት ትምህርት ውጤታማ እንዲሆን የመማር ማስተማር ሂደቱ ተማሪዎች ሃላፊነት ወስደው የራሳቸውን የመማር ሂደት እንዲመሩ የሚያበቃቸው እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ተማሪዎች የመማር ተግባራቸውን በሃላፊነት እንዲያከናውኑ ደግሞ የማንበብ ግለ ብቃት እምነታቸው ወሳኝነት ይኖረዋል (Schunk, 2003)፡፡

የአንብቦ መረዳት ዋና ጉዳይ ከቀረበው ፅሁፍ ውስጥ ተፈላጊ መረጃዎችን ለይቶ ማውጣትና መልዕክቱን በአግባቡ መረዳት መቻል ነው፡፡አንድን ጽሁፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የምንባቦቹ ይዘት ተነባቢ መሆኑ ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው Richard & Schmidit (2002) & Klare (1963) ይገልፃሉ፡፡ ይህም ማለት አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጽሁፍ ውስጥ የቀረቡ

አዳዲስ መረጃዎችን እንደሚፈለገው መጠን መገንዘብ መቻል ነው፡፡ጽሁፉ ሳቢና ተነባቢ የሚሆነው ደግሞ ምንባቦቹ የአንባቢውን ደረጃ ጠብቀው የቀረቡ እንደሆነ ነው፡፡

Feathers (2004) በበኩላቸው ይህንን ሀሳብ በማጠናከር ማንበብ ከምንባቡ ውስጥ በሚገኙ ፍሬ ነገሮችና በአንባቢው መካከል ያለመስተጋብር ነው ይላሉ፡፡ይህም የሚያሳየው አንብቦ መረዳት ከፍተኛ የሆነ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ በፀሐፊውና በአንባቢው መካከል የሠመረ ሀሳብን መጋራት እንዲኖር የሚያደርግ መሰረታዊ ዕውቀት መሆኑን ያመለክታል፡፡ Nuttall (1982) በበኩላቸው የአንብቦ መረዳትን ክሂል ስኬታማ ለማድረግ የተማሪዎች የግል ንባብ ወሳኝነት እንዳለው በአጽንዖት ይገልፃል፡፡ ከዚህ አባባል መገንዘብ የሚቻለው በትምህርት ቤትም ይሁን ከትምህርት ቤት ውጪ ዕውቀት የሚገኘው ተማሪዎች ባላቸው የማንበብና የመረዳት ችሎታ መጠን መሆኑን ነው፡፡ ዕውቀቱም የሚጎለብተው የቀረበውን ጽሁፍ ሀሳብ አንብቦ መረዳት ሲቻል በመሆኑ በማስተማሪያነት የሚዘጋጁት መጽሐፍት ዋና ዓላማም የሚቀርቡት የትምህርት ይዘቶች ማንበብ እንዲችሉ ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብ ይሆናል፡፡

አንብቦ መረዳት ቋንቋን፣ የቃል ንባብን፣ የቃል እውቀትንና ፍጥነትን መሰረት ያደረጉ ብዙ ውስብስብ የሆኑ ሂደቶችን በማዋሀድ ትርጉም የመፍጠሪያ መንገድ ነው (Paris 2005)፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳት በርካታ ውስብስብ ሂቶችን አዋህዶ እንደሚይዝና ትርጉም የመፍጠሪያ መንገድ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ እንደ Ahmadi and Pourhosein(2012) አገላለፅ አንብቦ መረዳት የአንባቢውን አጠቃላይ የቋንቋ እውቀትና ስለሚማረው የቋንቋ ይዘት እውቀት በጥምረት የሚኖረው የአዕምሮ ተግባር ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው አንባቢው ከሚያነበው ነገር ጋር በመግባባት የቀደመ እውቀቱን የሚፈትሽበት ነው፡፡

በመሆኑም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ለክሂሎች ትምህርት ስኬታማነት መርሃ ትምህርት አስፈላጊ ነዉ፡፡ መርሃ ትምህርት የአንድ የተወሰነ ትምህርት ንድፍ ወይም ቢጋር (outline) ነው፡፡

የመርሃ ትምህርትን ምንነት Ur (1996፣176) እና Cunningsworth (1989፣122) እንደሚያስረዱት መርሃ ትምህርት ከስርዓተ ትምህርት በጠበቀ መልኩ የአንድ ትምህርት አይነት ይዘቶችን ለማዋቀር በመነሻነት የሚያግዝ፣የትምህርቱን አጠቃላይ ዝርዝር አላማዎች የሚያሳይ፣የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ትምህርቱ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ የሚያመለክት እንዲሁም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና የግምገማ ስልቶችን የሚጠቁም ሰነድ ነው

በማለት ሲገልጹ በተመሳሳይም Widdowson (1990፣129) መርሃ ትምህርት ለመምህራን እንደመምሪያ እንደሚያገለግላቸው የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን በማሳየት፣የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደትን እንዴት እንደሚተገብሩ፣ለመምህራን መሪ የትምህርት መሳሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም መርሃ ትምህርት የአንድ ሀገር ቋንቋ የትምህርት መርጃ መሳሪያ አደረጃጀት፣ የመማሪያ መሳሪያ አዘገጃጀት፣ የመምህራን ፈተና እና ምዘና ስልቶችን፣ክፍሎች በአጠቃላይ አስፈላጊውን መረጃ የሚያገኙበት ከመርሃ ትምህርቱ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

እንደ Yalden (1987፣81) ገለጻ መርሃ ትምህርት በአንድ የትምህርት ተቋም በየክፍል ደረጃው የሚቀርብ ዝግጅት ሆኖ በየትምህርት አይነቱ የተቀነባበሩ ይዘቶችን፣የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ የመገምገሚያ መሳሪያዎችን የሚያመላክት መግለጫና ለመማር ማስተማሩ የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም ነው፡፡ በተጨማሪም ታላሚው አካል (ተማሪው) ከአካባቢው የሚያገኘውን የህይወት ልምድና እውቀት በመጠቀም የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ በተወሰነ ቦታና ጊዜ የሚሰራበት እቅድ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ መርሃ ትምህርት በአንድ የትምህርት ተቋም በየክፍል ደረጃ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያመለክት፣በተጨማሪም ለተማሪው የህይወት ልምድና እውቀት በመጠቀም የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያደርግ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

Dubin & Olshtain (1986፣79) ደግሞ መርሃ ትምህርት ተማሪው ምን መማር ይገባዋል ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ፣የሀገሪቱን አጠቃላይ የትምህርት ፍልስፍና እና የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲን መነሻ አድርጎ መምህሩ ማስተማር የሚገባውን፣ተማሪው መማር ያለበትን የሚገልጽ መሰረታዊ የቋንቋ ትምህርት ሰነድ ነው በማለት ይገልጻል፡፡

መርሐ-ትምህርት ማለት ደግሞ እጅግ መሠረታዊ የሆኑ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን የያዘ ፣ ቋንቋን መደበኛ በሆነ መልኩ ለማስተማር የሚያስችሉ መመሪያዎች ያሉት፣ በስፋትና በጥልቀት ከስርዓተ-ትምህርት ጠበብ የሚል ሰነድ ነው፡፡

Cupid Lucid, Hutchinson እና Waters (1987)ን ጠቅሶ በድህረ ገጹ ላይ እንዳሰፈረው መርሀ ትምህርት የትምህርት ዓይነቱን መለያ ባህሪ መሠረት በማድረግ ለመምህራንና ተማሪዎች መመሪያ ይሆን ዘንድ በባለሙያዎች የሚዘጋጅ የትምህርት መሣሪያ ነው፡፡ ድህረ ገጹ አክሎም መርሀ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎች ቀድመው ሊያስቡ የሚገቡ ግቦችን

በመጥቀስ ግቦቹን ከዳር ለማድረስ ሊከተሏቸው የሚገቡ ሂደቶችንና መመሪያዎችን የሚያመላክት ነው በማለት አትቷል፡፡ መርሀ ትምህርት አንድን የትምህርት ዓይነት (ኮርስ) ለማስተማር የሚረዱ ዓመታዊ፣ ወርሃዊ፣ ሳምንታዊና ዕለታዊ ክንውኖችን የሚጠቁም ሰነድ ነው፡፡ መርሀ ትምህርት በውስጡ በርካታ ዓብይና ዝርዝር ጉዳዮችን ያቅፋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ይዘት፣ ዓላማ፣ የክፍለ ጊዜ ቆይታ፣ ዓውደ ርዕስ፣ መርጃና ማጣቀሻ መጻህፍት፣ የመምህሩና የተማሪዎች ሚና፣ የግምገማ ስልት፣ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ በአጠቃላይ መርሀ ትምህርት የትምህርትን ዓላማ ከግምት በማስገባት በየክፍል ደረጀው ለሁሉም የትምህርት ዓይነት (ኮርስ) በታቀደና በተደራጀ መልክ ታስቦበት የሚዘጋጅ የትምህርት መሣሪያ ነው፡፡

ከምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው መርሃ ትምህርት የሀገሪቱን አጠቃላይ የትምህርት ፍልስፍና አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት መነሻ እንደሚያደርግና ለመምህሩ እና ለተማሪው አቅጣጫ የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡

በተጨማሪም መርሃ ትምህርት በትምህርት አይነቱ የተካተቱትን ይዘቶች አላማውን መሰረት አድርጎ ለመማር ማስተማሩ ስራ በሚያመች መልኩ በቅደም ተከተል የተደራጀ መመሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በ2014 ዓ.ም በተዘጋጀው የአስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌደራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ምን ያህል ዝምድና እንዳላቸው ለመፈተሽ ሞክሯል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ግዛዉ (2008) በ2001 ዓ.ም የተዘጋጁት የ9ኛና 10ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች በ2004ዓ.ም ከታተሙት የተማሪዉ መጻሕፍት ጋር ያላቸው የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ በሚል ጥናታቸው፣ "በ9ኛ ክፍልም ሆነ በ10ኛ ክፍል የሚገኙ ጥቂት ዓላማዎችና ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ ዉስጥ ያሉና በመማሪያ መጽሐፍቱ ዉስጥ ያልተካተቱ፤ እንዲሁም በመማሪያ መጽሐፍቱ ዉስጥ ኖረው በመርሃ ትምህርቱ ያልተቀመጡ ዓላማዎችና ይዘቶች አልፎ አልፎ መኖራቸው ተስተውሏል፡፡" በማለት በማጠቃለያ ክፍል ላይ ጠቁመዋል፡፡ ይህ መርሀ ትምህርቱ ላይና በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ ዓላማዎችና ይዘቶች ክፍተት መኖራቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም አሁን በአዲስ መልክ እንደፌዴራል ቋንቋ የተዘጋጀው አማርኛ

መማሪያ መጽሐፍ ይህንን ችግር ምን ያህል አስተካክሎና አርሞ እንደተዘጋጀ በጥናት አስደግፎ ማወቅ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

በተጨማሪም አጥኚዋ በረዥም ጊዜ የማስተማር ልምድ ቀደም ሲል በነበሩ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ የተለያዩ የመርሃ ትምህርትና የይዘቶች ተጣጥሞሽ ክፍተቶች የሚስተዋሉ መሆናቸውን ስትመለከት ስለቆየች አሁን አዲስ ተዘጋጅቶ እየተሰራበትና አገልግሎት እየሰጠ ባለው መርሃ ትምህርትና አስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ችግሮቹ ምን ያህል ተቀርፈው እንደተደራጁና እንደቀረቡ ለማሳየት ያላት ፍላጎት በዚህ ርዕስ ጥናት እንድታካሂድ አነሳስቷታል፡፡

## 1.3. የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች

ጥናቱ ለሚከተሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ አሰገኝቷል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. በአዲሱ የ10ኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ምን ያህል ነው?
2. በአዲሱ አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ግንኙነት አላቸው?

## 1.4. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉን ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ ሲሆን፣ በንዑስነት ደግሞ፡-

1. በአዲሱ የ10ኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው መማርያ መጽሐፍ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ መጠቆም፣
2. በአዲሱ አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት መመርመር ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

አንድ ጥናት ሲካሄድ ለተለያዩ አካላት የሚያስገኘው ፋይዳ ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህም ጥናት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

- በ10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ከዚህ ጥናት ዉጤት በሚያገኙት ፍንጭ መሠረት የመማር ማስተማር ሥራቸዉን እንዲያከናውኑ ያግዛቸዋል፡፡
- ለመርሃ ትምህርትና ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች ዳግሞ በዝግጅት ምዕራፍ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ በመጠቆም አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አረጃጀትን ደጋግመው እንዲከልሱና የማሻሻያ እርምት እንዲሰጡ ያስችላል፡፡
- ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት እና ተያያዥነት ባላቸዉ ጉዳዮች ላይ ወደፊት ጥናት ለሚያደርጉ አጥኚዎች እንደመነሻ እና ማጣቀሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ከይዘት አንጻር አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉን ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ መርሀ ትምህርት በርካታ ይዘቶች ያሉት ቢሆንም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በአንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ በጥናቱ የተተኮረበት መማሪያ መጽሐፍ አማርኛ እንደፌደራል በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በተዘጋጀው መጽሐፍ ነው፡፡ ከቦታ አንጻር ደግሞ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በሸካ ዞን ቴፒ ከተማ አስተዳደር ቴፒ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጥናቱ ትኩረት ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ዳሰሳ

ይህ ምዕራፍ የተለያዩ ክለሳ ድርሳናት የሚቀርቡበት እንደመሆኑ ከዚህ የጥናት ርዕስ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተለያዩ ጸሀፍትና ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት ያነሱትን ጽንሰ ሀሳቦች ለመዳሰስ ሞክሯል፡፡

### 2.1.1. የአንብቦ መረዳት ምንነት

የአንብቦ መረዳት ምንነትን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ሀሳብ ሰንዝረዋል::
Williams (1990፣2) እንደገለጹት አንድን ፅሑፍ አንብቦ መረዳት ሲባል በፅሑፉ ውስጥ የተፈለገውን መልዕክት በተቻለ መጠን መገንዘብ ነው፡፡በሌላ አገላለጽ የሚፈለገውን መረጃ ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ ፈልቅቆ ማውጣት የሚይዝ ነው፡፡ በተመሳሳይ Nuttal (2000፣28 ) አንብቦ መረዳት የጽሑፉን ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ አገላለጽ አንዱ አረፍተነገር ከፊተኛውና ከተከታዩ ጋር ያለውን የሀሳብ ግንኙነትና ግጥምጥምነት የሚፈጥሩ አያያዦች የጸሐፊው ሀሳብ የሚንጸባረቅባቸው በመሆናቸው ሊተኮርባቸው የሚገቡ ናቸው ይላሉ፡፡ በመሆኑም ከላይ ከተገለጹት የምሁራን ሀሳብ አንብቦ መረዳት ማለት የፅሁፉን መልክት መረዳት፣የፅሁፉን ቅደም ተከተል ሀሳብ ግንኙነት የሚፈጥሩ አያያዦች ትኩረት እንደሚገባቸው መረዳት ይቻላል፡፡
በሌላ መልኩ Green Wood (1981፣89) አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት መገንዘብ ነው፡፡ በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ያለን መልዕክት ለመረዳት ታዲያ የእያንዳንዱን ቃል ፍቺ ማወቅ የግድ አይደለም፡፡ በጽሑፍ ውስጥ በግልጽ የቀረበው መልዕክትና መልዕክቱን ለማጠናከር የገቡት ዝርዝር ጉዳዮችን መረዳት ግን አስፈላጊ ነው፡፡
እንደ Grellet (1981፣3-4) አገላለጽ ደግሞ አንብቦ መረዳት አንድ ጽሑፍ የያዘውን መረጃ መገንዘብ ቢሆንም አንብቦ የመረዳት ደረጃው ሊለያይ ይችላል፡፡ ይህም ከሚነበበው ነገር፣ ከሚነበብበት ዓላማ፣ ከአነባበብ ዘዴው መለያየት ሊከሰት ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- በአንድ ሰሌዳ ላይ የተለጠፈ ማስታወቂያና በአንድ መጽሐፍ ላይ የታተመ ሳይንሳዊ ጥናት በተመሳሳይ መንገድ አይነበቡም ይላሉ፡፡

ስለዚህ አንብቦ መረዳት ማለት በጽሑፍ ውስጥ የቀረበውን ሀሳብ ፍቺ ማግኘት እና ከሚነበበው ጽሑፍ ሀሳብን ማግኘት ነው፤ እንዲሁም አንብቦ መረዳት ጸሐፊው በጽሑፍ ያቀረባቸውን ፍቺ አዘል መልእክቶችን በአእምሮ ውስጥ ማያያዝና ማሰላሰል ነው ማለት ይቻላል፡፡

በሌላ መልኩ አንብቦ መረዳትን በሁለት ከፍለው የሚያስቀምጡ ምሁራንም አሉ፡፡ አንደኛው በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የሰፈሩ ጉዳዮች መገንዘብ ነው፡፡ በስሩም በጽሑፍ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና ሀሳቦች መገንዘብ፣ በግልጽ የሚታዩ ሁኔታዎችን፣ ክስተቶችን፣ድርጊቶችንና የመሳሰሉትን ቅደም ተከተል በማስታወስ ግልጽ የሆኑ አንድነቶችን እና ልዩነቶችን መለየት፣የምክንያትና ውጤት ትስስር ማስታወስ ወዘተ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎቹ ተጠየቃዊ እውቅናንና ግምትን በመጠቀም በጽሁፍ ውስጥ በግልጽ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው በማለት Grellet (1981፣ 51) እና Sheng (2000፣ 13-15) ገልጸዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው የምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው የምንባቡን ዋና ሀሳብ ለይቶ ማወቅ፤በጽሑፍ ውስጥ የሚታዩትን ነገሮች በቅደም ተከተል ማስታወስ፤የምክንያትና ውጤት ትስስርን በመገንዘብ ቀጥሎ ሊሆን የሚችለውን ነገር መገመት፤እንዲሁም በጽሁፍ ውስጥ በግልጽ ያልሰፈሩትን ሃሳቦች አንብቦ መረዳትን ያካትታል፡፡

እንደ Smith (1985፣ 24) አገላለጽ ደግሞ አንብቦ መረዳት አንባቢ ይዞት ለሚነሳው ጥያቄ መልስ ማግኘት ማለት ነው፡፡ የሚነበብን ጽሑፍ አስመልክቶ ጥያቄ መጠየቅ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ባህሪ ነው፡፡ አንባቢ ለሚጠይቀው ጥያቄ መልስ አገኘ ማለት በአንባቢው እና በጸሐፊው መካከል ተግባቦት መኖሩን ያሣያል፡፡ በጽሑፉና በአንባቢው መካከል ተግባቦት አለ ማለት የሚቻለውም መረዳት ሲኖር ነው ይላሉ፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳት ማለት በአንባቢው እና በጸሐፊው መካከል ተግባቦት ሲኖርና መረዳት ሲቻል መሆኑንን መገንዘብ ይቻላል፡፡

Grellet (1981፣4-5) በበኩላቸው አንባቢ በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙትን አያያዦች አገባብ፣ አገልግሎት እና ትርጉም መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህን መገንዘቡ ደግሞ የጽሁፉን መልዕክት ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው በማለት አንብቦ ለመረዳት አያያዦችን ሰዋሰዋዊ አገባብ እና ትርጉም መገንዘብ አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ አንብቦ ለመረዳት የአያያዦችን ሰዋሰዋዊ አገባብ ፣ትርጉምና አግልግሎት መገንዘብ እንዳለብን መረዳት ይቻላል፡፡

በአንብቦ መረዳት ውስጥ በርካታ ንዑሳን ክሂሎች እንዳሉ Sheng (2000፣12-15) በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡ አንደኛ የአንብቦ መረዳት ንዑስ ክሂል ቃላትና ሀረጋትን የመረዳት ነው፡፡ የቃላትና

የሀረጋትን ትርጉም በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ ከሰፈሩ መረጃዎች እና ፍንጮች በመነሳት ወይም በቅድመ እውቀት በመነሳት ወይም ሁለቱን በማቀናጀት የመረዳት አቅምን የማጎልበት ክሂል ነው፡ ፡ ለዚህም የቃላትና የሀረጋትን ቀጥተኛ መዝገበ ቃላዊ ትርጉም ከመረዳት ባሻገር አውዳዊ ፍቻቸውንም መረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ለአንብቦ መረዳት መሰረታዊ የሆኑ ፈሊጦችን፣ዘይቤዎችንና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ከገቡበት አውድ አንጻር መተርጎምና መረዳትም ትልቁ ክህሎትነው፡፡

ሁለተኛ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች የንባብ ስልቶች ናቸው፡፡እነሱም፡-

1. የገረፍታ ንባብ (Skimming)፡- አንድን ጽሁፍ ገረፍ ገረፍ አድርጎ በማንበብ ስለምን እንደሚያወራ ለማወቅ የሚደረግ ሂደት ነው፡፡
2. የአሰሳ ንባብ (Scanning)፡- አይንን በፍጥነት በማንቀሳቀስ አንድን ውስን መረጃ ለማውጣት ቀን፣ ስም፣ ዓመተ ምህረት፣ የመሳሰሉትን ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ ለማግኘት የሚደረግ የንባብ ስልት ነው፡፡
3. የፍጥነት ንባብ (Extensive Reading)፡-በፍጥነት በማንበብ የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ ለመረዳት የሚደረግ ስልት ነው፡፡
4. ጥልቅ ንባብ (Intensive Reading) ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የምንባቡን ሀሳብ በዝርዝር እና በጥልቀት ለመረዳት የሚደረግ ስልት ነው፡፡እነዚህን ስልቶች ጠንቅቆ በማወቅ በንባብ ጊዜ እንደየ አላማችን በመቀያየር መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ሶስተኛው የአንብቦ መረዳት ንዑስ ክሂል ቃላትን ወይም ሐረጋትን በልምድ ካዳበርነው እውቀት በመነሳት የመተርጎምና የመረዳት ክሂሎችን ማዳበር ነው፡፡ እነዚህ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን በሚገባ በማዳበር የአንብቦ መረዳት አቅምን በእጅጉ ይጨምራሉ፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ይዘቶች ያሏቸውን ምንባቦች አንብቦ በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላል፡፡

ከዚህ በላይ ያየናቸው ሀሳቦች እንደሚያመለክቱት አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚገኘውን ፍቺ መገንዘብ ብቻ ሣይሆን አዳዲስ መረጃዎችን ለቅሞ ለማውጣት እና ፍቺ ለመስጠት እንዲሁም በጽሁፉ በግልጽ ያልተቀመጡ ነገሮችን ለመተንበይ የሚደረግ ሂደት ነው፡፡ የጽሁፉን ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ ፍሰት መረዳት፣የአያያዦች ሰዋሰዋዊ አገባብ እና ትርጉም መገንዘብን እንደሚያካትትም መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.2. የመርሃ ትምህርት ምንነት

መርሃ ትምህርት የስርዓተ ትምህርት አነስተኛ ክፍል ሆኖ በስርዓተ ትምህርት ውስጥ የተጠቃለሉትን የትምህርት ፍልስፍናዎች ውስን አላማ ባላቸው ትምህርቶች ውስጥ የሚተረጉም፣ጥልቀት ያለውና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የመማር ማስተማር ክንውን ማመልከቻና ከስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የሚመጣ ነው በሚለው Stem (1983) እናYalden (1983) ይስማማሉ፡፡

Tagg and WoodWard (2011) በበኩላቸው በዘልማዳዊ ሰዋሰው ማስተማር ተለምዷዊ የነበረ ሲሆን፤መርሃ ትምህርት በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ሊሰጥ ከታሰበው በቀላሉ በቅደም ተከተል የተቀመጠ ሰዋስው ነው፡፡ ነገር ግን ብዙ ዘመናዊ መርሃ ትምህርቶች በመምጣታቸው ምክንያት የፍላጎቶች ትንተና እና የሌሎች የሰፊ ትንተና አይነቶች የመርሃ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት እንዲለወጥ አደረገው ይላሉ፡፡ በተጨማሪም በመርሃ ትምህርትና በስርዓተ ትምህርት መካከል ያለውን ልዩነት Richards (2001) እንዳስቀመጡት፣ልዩነታቸው ስፋት እና ጥልቀት ነው ይላሉ፡፡ እንዲሁም የብሪታኒያ መርሃ ትምህርት በስርዓተ ትምህርት ውስጥ እንደሚካተት ገልጸው ስርዓተ ትምህርት ሰፊ ይዘት እንዳለው አመልክተዋል፡፡

ለመርሃ ትምህርት መፈጠር እንደ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው በተለያዩ ጊዜያት ከቋንቋ ጥናትና ምርምር በመነሳት የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችንና የቋንቋ ማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎች በዓለም ላይ መከሰት እንደሆነ Richardsand Rodgers (2001) ይጠቁማሉ፡፡

ከላይ እንደተገለጸው መርሃ ትምህርቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለማስተማር በቀላሉና በቅደም ተከተል በማቅረብ ከማገልገሉም በላይ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የማስተማር መማር ክንውን ማመልከቻ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

### 2.1.3. የመርሃ ትምህርት አስፈላጊነት

መርሃ ትምህርት ተማሪው ምን ይማራል? ወይም ምን መማር ይገባዋል የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ የሚመልስ የትምህርት ሰነድ ነው፡፡ አስፈላጊነቱም ከነዚህ መሰረታዊ ጥያቄ የሚመነጭ ነው፡፡ Dubin እና Olshtain (1986፣32-38) እንደሚተነትኑት መርሃ ትምህርት በስርዓተ ትምህርት ላይ ተመርኩዞ የሚዘጋጅ የሥርዓተ ትምህርቱ መሰረታዊ ዓላማ ተከታይነት ባለው ሁኔታ ወደ ተግባር የሚተረጎምበት ሰነድ ነው፡፡

መርሃ ትምህርት ለመርሃ ትምህርትነቱ ብቻ እንደ ትምህርታዊ ሰነድ የሚዘጋጅ አይደለም። መርሃ ትምህርት Dubin እና Olshtain (1986፣3-15) እንደገለፁት አንድ የተወሰነ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራምን ከግብ ለማድረስ መርሃ ትምህርት መንደፍ የግድ አስፈላጊ በመሆኑ የሚዘጋጅ ነው። የመርሃ ትምህርትን አስፈላጊነት የሚገልጹ መሰረታዊ ጉዳዮችን Prabu (1987፣83-91) Dubin እና Olshain (1986) እንደ ሚከተለው ይገልጿቸዋል። እነዚህም፡-

1. የቋንቋን ረቂቅ ባህርይና ውስብስብነት ግምት ውስጥ በማስገባት ተማሪውን በአግባቡ እንዲማር የቋንቋ መምህሩም በተገቢው የማስተማር ክሂል እንዲጠቀም ለማድረግ መርሃ ትምህርት አስፈላጊ ነው።ምክንያቱም በመርሃ ትምህርት አማካኝነት ረቂቁና ውስብስቡ ቋንቋ ተመርምሮ ደረጃ በደረጃ ተሸንሽኖ /ተከፋፍሎ/ ይቀርባል።
2. መርሃ ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ዕቅዱን ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለውን ሂደት በትክክል ስለሚገልጽ የቋንቋውን ትምህርት አሰጣጥ በተመለከተ በተማሪውም ሆነ በመምህሩ በራስ የመተማመን ስሜት የሚፈጥር ሰነድ ነው።
3. የመርሃ ትምህርት አስፈላጊነት ከሚገልፁ እውነታዎች ውስጥ የሚጠቀሰው መርሃ ትምህርት መምህራን ቋንቋን ለምን እንደሚያስተምሩና ተማሪዎችም ለምን እንደሚማሩ በተዘዋዋሪ የሚገልጽ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች በየትኛው የቋንቋ ክፍል ላይ ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው።
4. መርሃ ትምህርት በትምህርት ተቋማት ለሚካሄደው አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ሥርዓት ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ሰነድ ነው።ከዚህም አንጻር ህብረተሰቡ በቁጥጥርና ክትትሉ ሂደትም እንዲሳተፍ በማድረግና በእቅዱ መሰረት እየተከናወነ እንደሆነ ለማወቅ የሚረዳ ሰነድ ነው።
5. መርሃ ትምህርት የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት ለማዘጋጀትና የማስተማሪያ መረጃ መሳሪያዎችን ለመምረጥ የሚረዳ መሳሪያ ብቻ አይደለም።ግን በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው ስለሚገባው የመልመጃ አይነት በማዘጋጀት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ነው።
6. ከትምህርት ተቋም እስከ ሀገር አቀፍ ድርሻ ያልተዥጎረጎረ፣ አንድ ወጥ የሆነና ደረጃውን የጠበቀ የቋንቋ ትምህርት ለመስጠት ወሳኝ ድርሻ ያለው ሰነድ ነው።

በቋንቋ ትምህርት ሂደት በመማር ማስተማሩ የስራ ክንውን በሚካሄድ እንቅስቃሴ የግምገማ ሥርዓት ለማዘጋጀት የሚያስችል የመመዘኛ መስፈርት ለማዘጋጀት ወሳኝ ሚና ስላለው

አስፈላጊ ነው። በአጠቃላይ መርሃ ትምህርት አስፈላጊነቱ የሚወሰነው ተማሪው የሚማርበትን መምህሩ የሚያስተምርበትን አቅጣጫ የሚያሳይ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት ዝግጅትን ስለሚወስን የትምህርት መርጃመ ሳሪያዎችን ለማዘጋጀት የፈተናና የግምገማ ሂደቶች የሚወሰኑበትን መስፈርቶች የሚያሳይ ሰነድ በመሆኑ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው።

### 2.1.4. የመርሃ ትምህርት ጥቅም

እንደ Ur (1998) አገላለጽ መርሃ ትምህርት ለአንድ የትምህርት አይነት በየክፍል ደረጃው ተመጥነው የሚቀርቡ አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎችን፣ ይዘቶችን፣ ክንውኖችን፣ የክፍለ ጊዜያት መጠንና ይዘትን ለማቅረብ አመቺ ሊሆኑ የሚችሉ ስነ-ዘዴዎችን የመምሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎችንና መገምገሚያ ስልቶችን የሚጠቁም ወይም በዝርዝር የሚያስረዳ ሰነድ ነው ይላሉ።

ስለዚህ መርሃ ትምህርት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን ይዘቶች ለማስተማር በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ነው። እንዲሁም የቋንቋው ትምህርት እንዴት ግቡን ይመታል በሚሉ ጉዳዮች ላይ እንደመመሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል መረዳት ይቻላል።

ሌላው Nunan (1988፣43) በበኩላቸው መርሃ ትምህርት የትምህርቱን ይዘት ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድና ከቅርብ ወደሩቅ፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እያደራጀ የሚያቀርብና ተማሪው ምን እንደሚማር እና መምህሩ ምን እንደሚያስተምር የሚገልጽ ሰነድ ነው።

መርሃ ትምህርት የይዘት ውሳኔንና አደረጃጀትን የሚመለከት፣ በግቦች ተግባራዊነት ላይ የሚያተኩር የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት መርህ ሆኖ የሚያገለግል ባጠቃላይም በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን ትምህርት ለማገዝ የተደራጀ የትምህርት መሳሪያ ነው በማለት Breen (1984) እና Prabbhu (1987) ይገልጻሉ።

ከላይ በቀረበው ገለጻ መርሃ ትምህርት ይዘቶች ተመርጠው በአግባቡ የሚደራጁበት፣በክፍል ውስጥ እንዲከናወን በተፈለገው ተግባር ላይ የሚያተኩር የትምህርቱን ሂደት አቅጣጫ በማመልከት የሚመራ መዝገብ ነው።

Robinson (2011) እንደገለጹት፣ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚዘጋጀው መርሃ ትምህርት የተግባራትን ቅደም ተከተል የያዙ ምዕራፎች ጥንቅር ነው። በሌላ አገላለጽ መርሃ ትምህርት ስራ ለሚበዛበት መምህር የሚሰራውን በቀላሉ ለማስታወስ የሚያስችል ወይም በቂ የዝግጅት ጊዜ

ለሌለው መምህር የሚሰራውን ዝርዝር ነገር ለማስታወስ የሚያስችል ነው፡፡ ነገር ግን ጥሩ መርሃ ትምህርት ከዚህም በላይ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተዘረዘሩት እንደምንረዳው መርሃ ትምህርት የትምህርቱ ይዘቶችና አላማዎች በየክፍል ደረጃው ተመጥነው የሚቀርቡበት ለይዘቶቹ አመቺ የሆኑ ክንውኖችን የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡

### 2.1.5. የመርሃ ትምህርት ዓላማዎች

የመርሃ ትምህርት ዓላማዎችን አስመልክቶ Hatchinson and Waters (1987፣65) እንደ ሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡

የቋንቋ ትምህርትን ለማስተማር በሚያመ ችመልኩ በመጽሐፍት ውስጥ በምዕራፍ ክፍሎች መጥኖ ለማቅረብ ይረዳል፣ለተማሪዎችና ለሌሎችም የሚመለከታቸው ትምህርቱ በአግባቡ የተዘጋጀና የታቀደ መሆኑን ያረጋግጣል፤ለተማሪዎችና ለመምህራን ትምህርቱ ከየት ወዴት እንደሚሄድ አቅጣጫ ያሳያል፤እንዲሁም  ተማሪዎች ምን መማር እንዳለባቸው ብቻ ሳይሆን ለምን እንደሚማሩም ጭምር ይናገራል በማለት ያብራራሉ፡፡

በሀገራችንም የቋንቋ መርሃ ትምህርቶች ተቀርጸው እየተሰራባቸው ነው፡፡በመርሃ ትምህርቶችም መሰረት መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍት ተዘጋጅተው በመጽሐፍቱና በመርሃ ትምህርቶቹ መካከል ያለው ተጣጥሞሽና ግንኙነት በይዘት ትንተና ተገቢነት ተረጋግጦ የመማር ማስተማሩ ሂደት እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት ይደረስበታል ተብሎ ከታሰበው ግብ አንጻር ሊፈተሽ ይገባል፡፡

### 2.1.6. የመርሃ ትምህርት አለባውያን (Elements of Syllabus)

በመርሀ ትምህርት ውስጥ የመማር ማስተማር ተግባራትን በተመለከተ እና በመምህራንና በተማሪዎች የሚፈጸሙ ዝርዝር ተግባራትን ማካተቱ የጎላ አስተዋጽኦ ይኖረዋል በማለት Carl Wenning (2009) የሚከተለውን ዘርዝረዋል፡፡ ይኸውም፡-

- ተማሪዎች ለመማር ማስተማር ስራው ስኬት ምን መያዝና መፈጸም እንደሚገባቸው ያሳውቃቸዋል፤
- የሚሰጠውን ትምህርት ከስርዓተ ትምህርቱ ጋር እንዴት አጣጥሞ ማካሄድ እንደሚቻል ያግዛቸዋል እንዲሁም

- ትምህርታዊ ዓላማዎችን እንዴት ከግብ ማድረስ እንደሚቻል እገዛው የላቀ ነው፡፡

እንደ Tufts (2013) በወጉ የተዘጋጀ መርሀ ትምህርት በረካታ ጉዳዮችን አካቶ እንዲይዝ ይመክራል፡፡

የሚከተሉት የጋራ የሆኑ ትምህርታዊ ይዘቶችንና ተግባራት እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡ '

### 2.1.6.1. **የትምህርት ገለፃ** (descriptions)

ይህ ክፍል ስለ ትምህርት ባህሪይ ቀጥተኛ ግልጽና አጭር ማብራሪያ በመደበኛ ቃላትና አገላለገጽ የሚሰጥበት ነው፡፡ ማብራሪያው ከ547 ቃላት በላይ ሊወሰድ አይገባም፡፡ (Social media dictionary: 2016)፡፡ የተነደፈው መርሀ ትምህርት ተግባር ላይ ሲውል ተማሪው የሚማረው ይዘትና የትምህርቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ይገለጹበታል፡፡ በዚህ ክፍል ተማሪዎች የቀረበውን ይዘት ለመማር ሊኖራቸው የሚገባው የቀደመ ዕውቀት (Pre-request) እና ከትምህርት የሚጎለብቱት እውቀትና ክህሎት ይጠቀሳል፡፡ ትምህርቱ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ትስስር ወይም ዝምድና እና ተማሪዎች የሚማሩበት ዋና ምክንያት ሊገለጽ ይገባል፡፡

### 2.1.6.2. **የትምህርት ዓላማዎች** (Learning objectives)

ይህ የተነደፈው መርሀ ትምህርት ሲጠቃለል ተማሪዎች እንዲያውቁ የሚጠበቀውን ጉዳይ ይመለከታል፡፡ ዓላማውም መሰረቱን የጠበቀና ግብ መቺ ሆኖ በግልጽ ቋንቋ መስፈር ይኖርበታል፡፡

ተማሪዎች ከተቀመጠው ትምህርታዊ ይዘትና ተግባር መጠናቀቅ በኋላ የሚቀስሙት ዕወቀት፣ ክህሎትና አመለካከት መለካት እንዲችል ተደርጎ ሊዘጋጅ ይገባዋል፡፡ ሲዘጋጅም ተማሪዎች ሊፈጽሟቸው በሚችሏቸው ትግበራ ላይ በመንተራስ ነው፡፡

በተመሳሳይ Laura (2011) "ተማሪዎች ከተቀመጠው ትምህርታዊ ተግባራት በኋላ የሚቀስሙት እውቀት የሚያዳብሩት ክህሎትና የሚጎለብቱት አመለካከት በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በአላማነት ይካተታሉ፡፡ በተጨማሪም ትምህርቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጥረው አዎንታዊ ለውጥ ምን ሊሆን እንደሚችል ይታቀዳል፡፡

### 2.1.6.3. **የትምህርት ይዘት** (course content)

መርሀ ትምህርቱ ተግባር ላይ ሲውል ለትምህርት የሚቀርበው ትምህርታዊ ይዘት ባለው የትምህርት ጊዜ ስፋት ልክ በቅደም ተከከተል ተሸንሽኖ መቅረብ ይገባዋል… ትምህርታዊ ይዘቶች በስርዓት ተደራጅተው ይቀርቡበታል (Barbara፣2004)።

### 2.1.6.4. **ስነዘዴ** (methodology)

ተማሪው ትምህርቱን የሚማረው እንዴት ነው? የሚለውን ጥያቄ ይመለከታል። ይህ መሰረታዊ ጥያቄ የማስተማሪያ ዘዴው ምን መምሰል እንዳለበት ይጠቁማል። የማስተማሪያ ዘዴው አመራረጥና የማስተማሪያ መረጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም ይገለጽበታል።

በዚህ ክፍል የመማር ማስተማር ስራው እንዴት ሊካሄድና ተማሪዎች እንዴት ሊማሩ እንደሚችሉ መገለጽ አለበት፣ ስነ ዘዴዎቹም ተለዋጭ ቢሆኑ ይመረጣል። በመርሃ ትምህርቱ የስነ ዘዴው ቢገለጽ ተማሪዎች ለመማር ምን ቅድመ ዝግጅትና ቁሳቁስ እንደሚያስፈልጋቸው ፍንጭ ይሰጣል (Carf Wenning 2009)።

ለምሳሌ፡- ገለፃ፣ የቡድን ውይይት፣ የቡድን ስራ ወዘተ በስነ ዘዴነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

### 2.1.6.5. **ተፈፃሚ ተግባራትና የጊዜ መርሀ ግብር** (Assignments and its calendar)

ይህ በመምህሩ ፍላጎት ላይ የሚመሰረትና በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ሊቀያየር የሚችል ነው። ምክንያቱም በመርሀ ግብር ዝግጅት ወቅት ይህን ወስኖ ማለፍ አስቸጋሪ ስለሚሆን ነው (Tami Strang፣ 2012)።

እንደ Barbara (2004) አገላለጽ ምን ያክል የግልና የቡድን ስራዎች ፈተናዎች፣ ሙከራዎች፣ የመስክ ላይ ተግባራት ወዘተ ሊፈጸሙ እንደሚችሉ መገለጽ ይገባዋል። ፈተናዎቹም ዝግ ወይም ልቅ ስለመሆናቸው፣ የሚለኩት የክህሎት አይነት የሚጥበት ቀን፣ ቦታና ሰዓት ሊጠቆም ይገባዋል።

### 2.1.6.6. **አስተራረምና የውጤት አሰጣጥ** (Grading system)

የተማሪዎች ትምህርታዊ እውቀትና ችሎታ እንዴት መገምገምና መመዘን እንደሚገባ ስልቱን በመጠቆም ረገድ መርሀ ትምህርት ወሳኝ ድርሻ አለው።

አብዛኞቹ ተማሪዎች (በተለይ አዋቂዎች) ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡት የመርሀ ትምህርት ክፍል ቢኖር አንዱ የምዘና ስልት ነው። ስለሆነም የማስተማር ስራው ከመጀመሩ በፊት በመርሀ

ትምህርቱ ውስጥ ግልጽነት ያለውና የማያሻማ የምዘና ስርዓት ሊካተት ይገባዋል (Laura 2011)፡፡

### 2.1.7. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነትና ባህሪ

የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ተማሪዎች ምንባቡን ምን ያህል አንብበው እንደተረዱት ለመገምገም የሚዘጋጁ ከመሆናቸውም ባሻገር የተለያዩ የንባብ ስልቶችን ተማሪዎች እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን የተለያዩ ምሁራን በሁለት ዓይነት ምድቦች ከፍለው ያስቀምጡዋቸዋል፡፡ የምድብ ምክንያታቸውን ስንመለከትም ከጥያቄዎቹ ማቅረቢያ መንገድ እና ካላቸው ውስብስብነት የሚመነጭ ነው፡፡ ከጥያቄዎቹ ማቅረቢያ መንገድ አንፃር ምርጫ ሰጭ ወይም ዝግ ጥያቄዎችና ድርሰታዊ ጥያቄዎች እንዲሁም ከባድ ወይም ውስብስብ ብለን እንከፍላቸዋለን፡፡

#### 2.1.7.1. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነት

**ሀ. ምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች**

እንደ Rivers (1981፣ 387), Atkins (1996፣171-173), Nuttal (1982፣128-133) ገለፃ ምርጫ ሰጭ ወይም ተጨባጭ መልስ ፈላጊ ጥያቄዎች ቀለል ያሉና የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚቀርቡ የጥያቄ ዓይነት ናቸው፡፡ በተለይ እነዚህ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማስታወስ አቅማቸውን ለማመልከት ይጠቅማሉ፡፡ በምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ስር የሚካተቱትን Nuttal (1982፣133) በሚከተለው መልክ ይከፋፍሏቸዋል፡፡

- **አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ጥያቄዎች፡-** ተማሪዎች ዓረፍተ ነገር እንዲያቀናብሩና አስተያየታቸውን እንዲሰጡ አይገደዱም፡፡ አዎ ወይም አይደለም እያሉ እንዲመልሱ ነው የሚጠበቀው
- **መጠይቃዊ ጥያቄዎች፡-** በዚህ ጥያቄ ውስጥ የሚጠየቁ ይዘቶች የሚያካትቱት የሰው ስሞች፣ የቦታ ስሞች ፣ ድርጊቶች በጊዜ የሚገለፁ ነገሮችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በእነዚህ የጥያቄ ዓይነት የሚመደቡት የጥያቄ መጠየቂያዎች ማን?፣ ምን?፣ የትኛው? ፣ መቼ?፣ የሚሉትን ናቸው፡፡
- **የምርጫ ጥያቄዎች፡-** ተማሪዎች ለተሰጣቸው ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ይበልጥ መልስ የሚመልሳቸው ይሆናል ብለው የሚያምኑበትን ምርጫ ይወስናሉ፡፡ የምርጫ ጥያቄዎች የአማራጫቸው ብዛት አራት ወይም ሦስት አልያም ሁለት ሊሆኑ

ይችላሉ፡፡ የምርጫ ጥያቄዎች ተማሪዎች የመረጡት የምርጫ መልስ ለምን ትክክል መልስ እንደሆነ ወይም ለምን ስህተት እንደሆነ በመመርመር ሰፋ ያለ ትምህርት ያገኙበታል፡፡ ተማሪዎች የሚመርጡት መልስ ስህተት ቢሆንም እንኳ ከስህተታቸው ለመማር ትልቅ ሚና አለው፡፡

❖ **የእውነት ሐሰት ጥያቄዎች፡-** በዚህ የጥያቄ ዓይነት ተማሪዎች መልስ የማግኘትና የማጣት ዕድላቸው ሀምሳ ሀምሳ ነው፡፡

❖ **የአዛምድ ጥያቄዎች፡-** እነዚህ ጥያቄዎች በሁለት ጎናዊ ረድፎች የተደረደሩ ቃላትን፣ ሐረጎችን፣ ዓረፍተ ነገሮችን፣ ቁጥሮችንና ምልክቶችን ወዘተ የማዋሀድ፣ የማዛመድ፣ የማያያዝና የማቀናጀት ክንውኖች የሚፈፀምበት የጥያቄ ዓይነት ነው፡፡ ተማሪዎች ለሁሉም ጥያቄዎች ሊያጣምሩ የሚችሉ ጥንዶችን ይፈልጋሉ፡፡

### ለ. ድርሰታዊ ጥያቄዎች

ድርሰታዊ ጥያቄዎች ከምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች ጋር ሲነፃፀሩ ከበድ ያሉ እና ውስብስብ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲያደራጁ፣ እንዲገልፁ፣ እንዲያዋህዱ፣ የአረፍተ ነገሮችን ግንኙነትና ዝምድና እንዲያጤኑ፣አጠቃላይ የምንባቡን ሁኔታ እንዲገነዘቡ ሀሳባቸውን እንዲመርጡና እንዲገመግሙ የሚጠይቁ የጥያቄ ዓይነት ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ከምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች የሚለዩበት ሌላው መለያ ባህሪያቸው ተማሪዎች የመሰላቸውን ሀሳብ በራሳቸው አገላለጽ የማቅረብ ሚና አላቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በምንባቡ መነሻነት የግል አስተያየታቸውን እንዲሰጡ በምንባቡ ያሉ አገላለጾችና አቀራረቦች በራሳቸው አባባል እንዲያቀርቡ ነፃነት ስለሚሰጥ የተማሪዎችን የግል ብቃት ጎልቶ እንዲታይ የማድረግ ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በድርሰታዊ ጥያቄ የሚካተቱ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ምክንያታዊ ወይም ሀሳባዊ ጥያቄዎች፡-** እነዚህ የጥያቄ ዓይነቶች የተሟላ መልስ ፈላጊ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም ለምንና እንዴት የሚሉትን የመጠየቂያ ብልሃቶች ይጠቀማሉ፡፡

### 2.1.7.2. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ባህሪ

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አንድን ንባብ ተከትለው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሲሆኑ የጥያቄዎቹ ዓላማም ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ መረዳት አለመረዳታቸውን ለመገንዘብና ለማወቅ እንጂ የምንባቡን ይዘት ለተማሪዎች ግልጽ እንዲሆን ለማስተማር የሚቀርብ አይደለም፡፡ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ይዘት መረዳት አለመቻላቸው የሚታወቀው ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች

ሲመልሱ ነው፡፡ Nuttal (1982፣125) Nunan (1989፣33):: ስለሆነም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ ምን ያህል እንደ ተገነዘቡት ለማወቅ የሚቀርቡ ሲሆን ቅለት ክብደታቸው የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም Nuttal (1982፣132) አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ የመልመጃ ጥያቄዎች ሊይዟቸው የሚገባ ባህሪያት እንደሚከተለው በየደረጃው ከፋፍለው ያስቀምጣሉ፡፡

***ሀ. ተንታኝ ጥያቄዎች፡-*** በዚህ አይነት የሚቀርቡ የመልመጃ ጥያቄዎች ከሚቀርበው ምንባብ በቀጥታ ቃል በቃል በመውሰድ መልስ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡

***ለ. ማገናዘብና ማቀናበር የሚሹ ጥያቄዎች፡-*** እንደ እነዚህ አይነት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከመጀመሪያው ከበድ ያሉ ናቸው፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን ከምንባቡ በማውጣት የተጠቃለለ ሀሳብ እንዲያቀርቡ የሚጋብዙ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ ያሉ ዓረፍተ ነገሮችን ለመገንዘብ አጠቃላይ የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ እንዲረዱ የሚያደርጉ የመልመጃ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

***ሐ. መመራመርን የሚሹ ጥያቄዎች፡-*** በዚህ አይነት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ምንባቡን ደግመው በመስመር እንዲያነቡ የሚጋብዙ ናቸው፡፡ ከላይ የተገለጹት የጥያቄ አይነቶች በጣም ከባድ የሚያደርጋቸው ተማሪዎች የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ በዝርዝር ለማግኘት የግድ ምንባቡን በጥልቀት እንዲመረምሩ የሚያደርጉ በመሆናቸው ነው፡፡

***መ. የግምገማ ጥያቄዎች፡-*** የዚህ አይነት ጥያቄዎች ተማሪዎች ምንባቡን አንብበው አጠቃላይ ፍሬ ሀሳቡን በመገንዘብ የራሳቸውን አስተያየት እንዲሰጡ የሚጋብዙ ናቸው፡፡ በዚህ አይነት የሚቀርቡ መልመጃዎች የጸሐፊውን አቀራረብ፣ የምንባቡ ተአማኒነት፣ ስነ ጽሁፍም ከሆነ አቀራረቡን ይበልጥ ለመገምገም የሚያስችሉ የጥያቄ ባህሪይ ያላቸው ናቸው፡፡

***ሠ. የግል አስተያየቶችን የሚጠይቁ ጥያቄዎች፡-*** በዚህ አይነት የሚቀርቡ የመልመጃ ጥያቄዎች ደራሲው ወይም ጸሐፊው የሰጠውን መልስ ለማንጸባረቅ የሚጋብዙ የተማሪውን የግል አስተያየትና አመለካከት የሚጠይቁ ናቸው፡፡

ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች በየደረጃው ተዘጋጅተው ሊቀርቡ እንደሚገባ ነው፡፡ እነዚህ የሚመረጡ ይዘቶችም ከተማሪዎች አቅምና ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ ሲሆኑ የአንብቦ መረዳት አላማውም ውጤታማ ይሆናል፡፡

### 2.1.8. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አደረጃጀት

ተስፋዬ (1995) ዓለም እሸቱና ሳህሉ አክሊሉ (1992፣11)ን ጠቅሰው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን በሁለት አብይት ክፍሎች መድበው አቅርበዋቸዋል፡፡ የምንባቡን አጠቃላይ የአቀነባበር ወይም የአደረጃጀት መንገድ እንዲገልጹ ማድረግ አንደኛው ክፍል ነው፡፡ በዚህ ስር የምንባቡን ተግባር የሚጠይቁ ማለትም መዘርዘራዊ፣ ቀስቃሽ ወይም ኪነታዊ፣ መሆኑን መለየት የሚጠይቁ ሆነው ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡

ሁለተኛው ክፍል የምንባቡን ይዘት እንዲያብራሩና እንዲገልጹ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ማዘጋጀት ነው፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ደግሞ ግልጽ የሆኑና ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን መጠየቅ፣ በውስጠ ታዋቂነት የተገለጹ ጉዳዮችን በምንባቡ መሰረት መጠየቅ፣ በግምት ወይም በይምሰል ሊደረስባቸው የሚችሉትን ትርጉሞች መጠየቅ፣ በምንባቡ የቀረበውን ሀሳብ መገምገም፣ ማመዛዘን የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ሲደራጁ የምንባቡን ተግባር፣ የምንባቡን አይነት እና ይዘት በሚያብራራ መልክ ተዘጋጅተው ሊቀርቡ ይገባል፡፡

### 2.1.9. የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አዘገጃጀት

እነዚህ መልመጃዎች የንባብ ትምህርት ከተከናወነ በኋላ የቋንቋ ክሂሎችንና ይዘቶችን መለማመድ እንዲሁም የተለያዩ የመማሪያ ዕውቀቶችን ለመቅሰም ይቻል ዘንድ የሚዘጋጁ ተግባራት ናቸው፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አዘገጃጀት ወይም አቀራረብ በተለያዩ መንገድ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በምርጫ፣ በእውነት ወይም ሀሰት በል፣ በክፍት አጠያየቅ፣ ቅደም ተከተልን ማስተካከልና ሌሎችም ማቅረቢያ ዘዴዎች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ጥያቄዎቹ የሚቀርቡበት መንገድ የተለያዩ ሊሆኑ ቢችሉም እነዚህ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ግብ መቺ መሆን እንዲችሉና አቀራረቡ ምን መምሰል እንዳለበት የተለያዩ የመስኩ ምሁራን Nuttal (1996)፣ Grellet (1991)፣ Davies( 1995)ን በመጥቀስ የሚከተሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ማዘጋጀት እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡

- ጥያቄዎቹ ምንባቡን ባላነበቡ ሰው ሊመለሱ የሚችሉ ሊሆኑ አይገባም፡፡
- ጥያቄዎቹ በአንድ በተወሰነ የምንባቡ ክፍል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆኑ ሁሉንም የምንባቡን ክፍል በሚያስቡበት መንገድ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ሊመረመር ይገባል፡፡
- የጥያቄዎቹ ቁጥር ሳይበዛና ሳያንስ በቂ መሆኑ እየተረጋገጠ መዘጋጀት አለበት፡፡
- ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ምንባቡን በበለጠ እንዲረዱ የሚያግዙ መሆን አለባቸው፡፡

- ጥያቄዎቹ የተገለጹበት ቋንቋ ከምንባቡ ቋንቋ የጠነከረ፣ የጠጠረና የከበደ መሆን አይኖርበትም፡፡
- የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ ተማሪው በደረጃው ሊኖረው ከሚገባው የቋንቋ ብቃት የሚልቅ የቋንቋ አጠቃቀም መጠቀም የለባቸውም፡፡
- ጥያቄዎቹ በአቀራረባቸው የተለያዩ የማቅረቢያ መንገዶችን ተከትለው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምረው የሚቀርቡበትን መንገድ ማፈላለግ አስፈላጊ ነው፡፡

በተጨማሪም Connings worth (1995)ን በመጥቀስ መልመጃዎች በሚዘጋጁበትና በሚደራጁበት ወቅት ታሳቢ መሆን ያለባቸውን ጉዳዮች ገልጸዋል፡፡

- ግልጽ ከሆነ መመሪያ ጋር የሚቀርቡ መሆን መቻል አለባቸው፡፡
- ለመተግበር በቅድሚያ መመሪያዎቹን መከተል የሚያስችል ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
- የማንበብ ክሂሎችን ማዳበር የሚያስችሉ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
- መልመጃዎች ትምህርቱን ማጠናከሪያ እንጂ መገምገሚያ ብቻ መሆን የለባቸው፡፡ ተተግባሪ ሊሆን ይገባል፡፡
- መልመጃዎች ሲቀርቡ አንድ የአቀራረብ መንገድ ብቻ መከተል የለባቸውም፡፡
- ከሚመደበው የክፍለጊዜ ምጣኔ ጋር የተመጣጠኑ መሆን መቻል አለባቸው፡፡
- ከተማሪው የቋንቋ አጠቃቀም አንጻር የተገናዘቡና ክሂሎችን አዋህደው የያዙ መሆን መቻል አለባቸው፡፡
- የተማሪዎችን የዕድሜና የብስለት ደረጃ ያማከሉ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
- ከተማሪዎች ችሎታ አንጻር የተገናዘቡ መሆን አለባቸው፡፡
- ተማሪዎችን ለስራ ወይም ለተግባር የሚገፋፉ ሳቢና ማራኪ መሆን አለባቸው፡፡
- ለተማሪዎቹ ደረጃ የሚመጥኑ ዘዴዎች በመጠቀም የምንባብ ጥያቄዎች ሊቀርቡላቸው ይገባል፡፡

ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት የሚቻለው አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ መልመጃዎች በመጠናቸው በቂ፣ በአይነታቸው የተለያዩና ባላነበበ ሰው ሊመለሱ የማይችሉ መሆን እንዳለባቸው ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ጥያቄዎቹ የቋንቋ ክሂሎችን ሊያዳብሩ የሚችሉ እንዲሁም

ጥያቄዎቹ በቃላት አጠቃቀም ከምንባቡ ከበድ ብለው መቅረብ እንደሌለባቸው በመጠኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡

### 2.1.10. የአንብቦ መረዳት ችሎታን መለካት

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት ዋናው መሳሪያ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና እንደሆነ የመስኩ ምሁራን Madson (1983፡ 76)፣Weir (1990፡43) እና Stavens (1993፡ 481) ይስማማሉ፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመፈተን ተመርጠው የሚቀርቡ ምንባቦች ከመማሪያ መጽሐፍት፣ ከልቦለዶችና ኢ-ልቦለዶች፣ ከመጽሔቶች፣ ከጋዜጦች ወዘተ የተወሰዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ሂደት የሚመረጡ ፅሑፎች ግን በቅርበት ስለሚገኙ ብቻ የተወሰዱ ሊሆኑ አይገባም፡፡ ለመስራት ያላቸው አመችነት ሊጤን ስለሚገባ በተጨማሪም ምዘናው አስተማማኝ ይሆን ዘንድ ከአንድ በላይ የሆኑና በቂ መረጃዎችን በውስጣቸው የያዙ ምንባቦችን በመጠቀም ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎቹ የማንበብ ፍላጎት ከምንባብ ምንባብ ሊለያይ ይችላልና፡፡ ስለዚህም ከአንድ በላይ ምንባቦችን መጠቀም አስተማማኝነትን የሚጨምር በመሆኑ በእጅጉ የሚደገፍ ነው፡፡ የአንዱ ፈተና ደካማ ጎን በሌላ የፈተና አይነት ጠንካራ ጎን ይካካሳልና ሲሉ Madson (1983) ያመለክታሉ፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን አስመልክቶ Grellet (1996) እንደገለጹት የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ለመለካት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጅ ተማሪዎች በቀላሉ የሚረዱትና የተለያዩ አይነት መሆን አለባቸው፡፡ ጥያቄዎቹም ከተዘጋጀው ምንባብ ጋር ጥብቅ ዝምድና ያላቸው እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡ ይህ ጥልቅ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥያቄው ሲዘጋጅ የደራሲው አመለካከት ትኩረትና ድምጸት ሙሉ ዝንባሌ ሊሰጠው ይገባል፡፡ የጥያቄዎቹም አይነት በምርጫ፣ እውነት ሐሰት፣ በክፍት ጥያቄዎች ወዘተ ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡

መምህራን የአንብቦ መረዳት ፈተናን ሲያዘጋጁ ሶስቱን የአንብቦ መረዳት ደረጃዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው ሲሉ Karlin (1981) እንደሚከተለው በዝርዝር ይገልጻሉ፡፡

1. ቀጥተኛ ትርጉምን መረዳት(Litral Comprehension)፡-ቀጥተኛ ትርጉም መረዳት የታወቀ የአንብቦ መረዳት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ማንበብ የሚጠበቀው ላይ ላዩን ነው፡፡ መምህራንም ሊጠይቁት የሚገባ ጥያቄ በግልጽ የሰፈረን ሀሳብና መረጃን ይሆናል፡፡በዚህ ደረጃ የቃላት እውቀትንም መፈተን ይቻላል፡፡

2. አውዳዊ ፍችን መረዳት መቻል (Interpretive Comprehension):-ይህ ደረጃ በቀጥታ ከሰፈረው ትርጉም በዘለለ ጠለቅ ያለ መረዳትን ወይም ትርጉምን ይጠይቃል፡፡ የተማሪዎችን በጥልቀት ማንበብና ያነበቡትንም ነገር በጥንቃቄ የመገንዘብ ብቃትን ይፈልጋል፡፡ በጽሁፍ ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች ዝምድናንም በተገቢው መንገድ መለየት ያሻል፡፡ በዚህ ጊዜ የተማሪዎችን የአስተሳሰብ ደረጃም ምንባቡን ተመርኩዞ መለካት ይቻላል፡፡ አንብበው ከጨረሱ በኋላ የማጠቃለል፣ የማደራጀትና የመተንበይ ወዘተ ተግባር ያከናውናሉ፡፡ በዚህ ደረጃ መምህራን በጣም ፈታኝ የሆኑ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የጽሁፉን ሀሳብ መልሳችሁ አደራጁ፤ ስለ ርዕሱ ገለፃ አድርጉ፣የጸሐፊውን ዓላማ ግለጹ ጽሁፉን በራሳችሁ አገላለጽ አጠቃሉ የመሳሰሉት ጥያቄዎች ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡
3. ጥልቅ ንባብ (Critical Reading Comprehension)፡- በዚህ ደረጃ ሀሳቦችንና መረጃዎችን የመገምገሚያ ጥያቄ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ጽሑፉን በጥልቀት አንብቦ ዋና ዋና ሀሳቦችንና መረጃዎችን የመረዳት ብቃት ይጠይቃል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ የግል አስተያየትና እውነታን መለየት፣ተጨባጭ ነጥቦችን መለየት ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን ከጽሁፉ ውስጥ ለይቶ ማውጣት ወዘተ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

### 2.1.11. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥን በተመለከተ Narayanaswamy (1975፣ 144) Kaval (1979: 27) እናNuttall (1982፣ 37) መስፈርቶችን አስቀምጠዋል፡፡

Narayanaswamy (1975፣144) እናNuttall (1982፣37) በተሰጠው አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ተፈታኙ ከ100% ያገኘውውጤት 70% እንደሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታው በቂ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም Narayanaswamy (1975፣ 144) ተፈታኙ ከበቂ ፍጥነትጋር 70% ማግኘት ይገባዋል፡፡ የተፈታኙ ውጤት ከ70% በላይ ከሆነ ጥሩ ችሎታ አለው ማለት ይቻላል፡፡ ውጤቱም 50% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ ግን ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ እንደ Kaval (1979፣ 27) ደግሞ አንድ ተማሪ በአንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ከ75%- 90% ያገኘ እንደሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታው በቂ የሚባልበት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ተፈታኙ 90% ወይም ከዚያ በላይ ካገኘ አንብቦ የመረዳት ችሎታው ከፍተኛ ነው፡፡ ውጤቱ ከ75% በታች ከሆነ ግን ዝቅተኛ ነው በማለት አስቀምጠዋል፡፡

ይህም ችሎታው በቂ ደረጃ ላይ ለመድረስ የተፈታኙ ውጤት ከ75% በላይ መምጣት እንዳለበት ያሣያል።

ከላይ ምሁራኑ ያስቀመጧቸውን መስፈርቶች መነሻ በማድረግ ለተማሪዎቹ በሚሰጣቸው የችሎታ መለኪያ ፈተና ውጤት መሰረት ከ91%- 100% በጣም ከፍተኛ፤ከ81%- 90% ከፍተኛ፤ከ70% - 80% በቂ (መካከለኛ)፤ከ51%-69% ዝቅተኛ፣ 50% እና ከዚያ በታች በጣም ዝቅተኛ ብሎ መበየን ይቻላል።

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለመስራት የተለያዩ ልምድና ስልቶችን ለማወቅ ከራሷ የጥናት ርዕስ ጋር ተመሳሳይነት ያለቸውን በተለያዩ ጊዜያት የተሰሩ ቀደምት ጥናታዊ ጽሁፎችን ማየትና መፈተሽ የግድ መሆኑን በመረዳት በርካታ ጥናታዊ ጽሁፎችን ለመቃኘት ሞክራለች። በዚሁ መሠረት የአጥኚዋ የጥናት ትኩረት አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ ላይ ሲሆን አጥኚዋ ለጥናታዊ ምርምር ስራዋ እንዲረዳት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች ቃኝታለች።

ግዛው (2008) በ2001 ዓ.ም የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች በ2004ዓ.ም ከታተሙት የተማሪዉ መጻሕፍት ጋር ያላቸዉ የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል ለድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ያደረጉት ጥናት መርሀ ትምህርቱን ከዓላማና ከይዘት አንጻር የሚፈትሽ ሲሆን ከዚህ ጥናት ልዩ የሚያደርገው ይህ ጥናት በአንብቦ መረዳት ችሎታ መልመጃዎች ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆኑ፣ የተጠናበት ጊዜና ቦታ፣ ይህ ጥናት የሚጠቀመው የጥናት ንድፍ ተዛምዷዊ ሆኖ የግዛው ጥናት የተጠቀመው ገላጭ ንድፍ መሆኑ ሲሆን የሚያመሳስላቸው ደግሞ ሰነድ ምርምራንና ቃለ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት መጠቀሙ ነው።

አበበ እና ሌሎቹ (2008) የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ከመማሪያ መጽሀፉና ከመርሃ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በወሎ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ያካሄዱት ጥናታዊ ጽሑፍ መርሀ ትምህርቱ ከሰዋሰው ጋር ያለውን

ዝምድና የሚፈትሽ ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ የሚፈትሽ መሆኑ፣ የተጠቀሙት የጥናት ንድፍ ገላጭ ሆኖ ይህ ጥናት ተዛምዷዊ ንድፍ የተጠቀመ መሆኑ፣ ጥናቱ የተካሄደበት ጊዜና ቦታ፣ መረጃን ለመሰብሰብ መዛግበብት ፍተሻ ብቻ መጠቀማቸው ከዚህ ጥናት ልዩ የሚያደርግ ሲሆን መርሀ ትምህርቱን እንደ አንድ የጥናት ተለዋዋጭ ማድረጉ፣ ለጥናቱ የመረጃ ምንጭነት የተጠቀሙት አስረኛ ክፍል መጽሐፍ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል፡፡

ይመኙሻል (2014) የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አዘገጃጀትና አቀራረብ ፍተሻ (በ2007 ዓ.ም በታተመው የ5ኛ ክፍል እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድኅረ-ምረቃ መርሃ-ግብር በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነ-ዘዴ የአርቲስ ማስትሬት ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ፣ የተካሄደበት ጊዜ፣ እንዲሁም ይመኙሻል ለጥናቷ የተጠቀመችው የምርምር ንድፍ ገላጭ ሲሆን በዚህ ጥናት ተግባራዊ የተደረገው የጥናት ንድፍ ተዛምዷዊ መሆኑ፣ በዋናነት የይመኙሻል ጥናት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አዘገጃጀትና አቀራረብ ፍተሻ ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ የሚፈትሽ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያለያየው ሲሆን የሁለቱም ጥናቶች ትኩረት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችን ከመርሀ ትምህርት ጋር ያለውን ግንኙነት የሚፈትሽ መሆናቸው፣ ሁለቱም ጥናቶች ሰነድ ፍተሻንና የመምህራን ቃለ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀሙ መሆናቸው ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፤ የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት ጥናቱ መሠረት ያደረገው ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍን ሲሆን የተገኘውን መረጃ በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተንትኗል፡፡ መጠናዊ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት እንደ ያለው (2009፤18-20) መጠናዊ የምርምር ዘዴ ደግሞ የችግሩ መጠን ምን ያህል ነው የሚለውን ጥያቄ በቁጥር ተንትኖ የሚመልስ በመሆኑ ነው፡፡

## 3.2. የጥናቱ መረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት በዋናነት ያተኮረው በ2014 ዓ.ም በአዲስ መልክ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ነው፡፡

ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት የዋሉት በ2014 ዓ.ም እንደፌዴራል በአዲስ መልክ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣ በ2014 ዓ.ም እንደፌዴራል በአዲስ መልክ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ የመምህር መምሪያ መጽሐፍ እና በ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በቴፒ ከተማ አስተዳደር በቴፒ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን እያስተማሩ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡

## 3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

### 3.3.1. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ስኬት ተገቢ መረጃ እንዲሰጡ የተመረጡት በ2016 ዓ.ም በቴፒ ከተማ አስተዳደር በቴፒ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስረኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያስተምሩ ሦስት (3) መምህራን በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

### 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተግባራዊ የተደረጉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

#### 3.4.1. የሰነድ ፍተሻ

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት የዋለው ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ይኸውም በአዲሱ የአስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መልመጃዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ ለመፈተሽ ይረዳ ዘንድ የአስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ እና አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ አገልግሎት ላይ የዋሉ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መልመጃዎችን ለመረጃ ምንጭነት ለመጠቀም አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን የመምህሩ መምሪያ ደግሞ ተገቢነታቸውን በመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ ግቦችን ለመረጃ ምንጭነት ለመጠቀም አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

#### 3.4.2. ቃለ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት ከዋሉት መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ቃለ መጠይቅ ሌላኛው ነው፡፡ ቃለ-መጠይቅ ተመራማሪው ከባለ ጉዳዩ ጋር በግንባር በመገናኘት በቃል የሚያደርገው ውይይት ነው፡፡ እንደ ያለው (2009፤183) ገለጻ ቃለ መጠይቅ በአብዛኛው ውስን ለሆኑ ተጠያቂዎች ሊቀርብ የሚችልና ጥናት የሚካሄድበትን ርእሰ ጉዳይ አስመልክቶ ጥልቅ እና የተብራራ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ጠቃሚ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በቃል መጠይቅ ጊዜ ተጠያቂው ያልተረዳው ነገር ቢኖር እንኳን ማብራሪያ የሚያገኝበት ሰፊ እድል ስላለ መላሹ ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃዎችን ለመስጠት ያስችለዋል ፡፡እንዲሁም ቃለ መጠይቁ የመምህራን ዳራዊ መግለጫዎችን አካቶ ይይዛል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መልመጃዎችን ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ ለመፈተሽ ታላሚውን ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን መረጃውን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## 3.5. የመረጃ አደረጃጀት

የጥናቱ ትኩረት አዲስ በተዘጋጀው የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ሲሆን የሚያስፈልጉ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻ ከተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ እና መምህሩ መምሪያ መጽሐፍ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ ከሚያስተምሩ መምህራን መረጃዎቹ ተሰብስቧሉ፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በዓይነት ከተደራጁ በኋላ ትክክለኛነታቸው የማረጋገጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡

በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎችን ወደ ቁጥር የመቀየር ሥራ ተከናውኗል፡፡ በመቀጠል የተገኙት መረጃዎችና የመርሀ ትምህርቱን ንጽጽር በተገቢው መተንተኛ ዘዴ የመተንተን ሥራ ተከናውኗል፡፡

## 3.6. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አዲስ በተዘጋጀው የአስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች የተሰበሰቡ መሆናቸው ከፍ ሲል ተገልጿል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንታኔ ከመጀመራቸው በፊት መረጃዎቹ በትክክል ስለመሞላታቸው ተረጋግጧል፡፡ በመቀጠልም በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በመጠናዊ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ ተዛምዷቸውን ለመለካት በ(SPSS) ሶፍት ዌይር የፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ (Pearson Correlation Coefficient) በመጠቀም በመቶኛ ተሰልቶ በንጽጽር (Ratio) ቀርቧል፡፡ የትንተናው ሂደትም በቃለ መጠይቅ ከመምህራን የተገኙ መረጃዎችን እንደ አስፈላጊነታቸው ጥቅም ላይ በማዋል በመጀመሪያ በተተኳሪ መርሃ ትምህርት እና መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መልመጃዎች ተጣጥሞሽ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የመረጃ ትንተና

ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ ነው። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በምዕራፍ ሶስት ላይ እንደተገለጸው አገልግሎት ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ በዋናነት ሰነድ ፍተሻ ሲሆን በአጋዥነት ጥቅም ላይ የዋለው ደግሞ ቃለ መጠይቅ ነው።

የዚህ ክፍል ዓላማም የተሰበሰቡትን መረጃዎች በተገቢው መንገድ መተንተን ሲሆን በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በቅደም ተከተላቸው በዚህ ክፍል ተተንትነው ቀርበዋል።

### 4.1.1. ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ ትንተና

ለሰነድ ፍተሻው በዋናነት Tufts (2013) በወጉ የተዘጋጀ መርሀ ትምህርት በረካታ ጉዳዮችን አካቶ እንዲይዝ ይመከራል ሲሉ የገለጻቸው የመርሀ ትምህርት አላባውያን እንደ መለኪያ ያገለግላሉ። እነሱም፡- ተገቢ ገለጻ ስለመሰጠቱ፣ ተገቢ ዓላማ ስለመነደፉ፣ ተማሪዎች የሚሠሯቸው ተግባራት ስለመቅረባቸው፣ የማስተማሪያ ስነዘዴዎች ስለመካተታቸው፣ የጊዜ መርሀ ግብር በየክፍለ ጊዜ ተሸንሽኖ ስለመቅረቡ እንዲሁም ተገቢ የምዘና ዘዴዎች ስለመቅረባቸው የሚሉት ሲሆኑ እና በተጨማሪ በቃለ መጠይቅ አስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ከሚያስተምሩ መምህራን የተሰበሰቡ መረጃዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል።

#### 4.1.1.1. አዲሱ አስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌደራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አጠቃላይ መግለጫ

በ2014 ዓ.ም አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ የተዘጋጀው የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር እና በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ አጋሪነት ታትሞ ሥራ ላይ የዋለ ነው።

መጽሐፉ የተሰናዳው ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሐትምህርት መሠረት አድርጎ ነው፡፡ ተማሪዎች በደረጃቸው የተለያዩ ባህላዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ዓለማቀፋዊ፣ ወዘተ. ይዘቶችን/ እሴቶችን በአማርኛ ቋንቋ እንዲገልጹ ስለሚጠበቅ፣ መጽሐፉ ለይዘቶችም ከክሂሎች ያልተናነሰ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የዚህም ዋና ዓላማ ተማሪዎች በምንባቦች አማካይነት የንግግርና የማዳመጥ፣ የንባብና የጽሕፈት ክሂሎቻቸውን፤ የቃላትና የሰዋስው ዕውቀታቸውን እንዲሁም የሥነጽሑፍ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዝ ነው፡፡ መጽሐፉ ከሕይወት ተሞክሮ ጋር የተዛመደ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ አዳዲስ ጉዳዮችን ለመማር ግላዊ ገጠመኞቻቸውንና ልምዶቻቸውን እንዲጠቀሙ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሠረት ችግር ፈቺና አሳታፊ ተግባራትና መልመጃዎች በየምዕራፎቹ ተካተዋል፡፡ ተግባራቱም ተማሪዎቹ ቋንቋውን በተለያየ መንገድ እንዲጠቀሙበት የሚያስችሉ ናቸው፡፡

መጽሐፉ በጠቅላላ 109 ገጾች ያሉት ሲሆን በቀዳሚ ገጽ በዝግጅት ወቅት አስተዋጽኦ የነበራቸውን የተለያዩ አካላትን በማመስገን በመጀመር ወደ ምዕራፎቹ ከመግባቱ አስቀድሞ በመግቢያ ክፍል የቋንቋ ትምህርት ዓላማን እና ዓላማዎችን ለማሳካት ያካተታቸውን ጠቅላላ ይዘቶች፣ እንዲሁም መጽሐፉ እንዲለወጥ የተፈለገበትን ዓላማ በማብራራት ቀርቧል፡፡

መጽሐፉ በጠቅላላ አስር (10) ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ሁሉም ምዕራፎች ትምህርቱ ከመቅረቡ በፊት የትምህርት ዓላማን ቀዳሚ አድርገው የቀረቡ ናቸው፡፡ በሁሉም ምዕራፎች ስር የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የቃላት እና የሰዋስው መልመጃዎች ተካተዋል፡፡ እነዚህን መሠረታዊ የቋንቋ ክሂሎችንና የስነ ልሳን ዘርፎችን ለማስተማር ያለሙ የተለያዩ ምንባቦችና ማስተማሪያዎች ቀርበዋል፡፡

መጽሐፉ በሁሉም ምዕራፎች መጨረሻ የምዕራፉ ማጠቃለያ፣ የክለሳ ጥያቄዎች እና የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጾች ተያይዘው ቀርበዋል፡፡ መማሪያ መጽሐፉ በመጨረሻው ክፍል ተገቢ ዋቢ ጽሑፎች የቀረቡለት ሲሆን በተጨማሪም የአማርኛ ቋንቋ የፊደል ገበታ እና የግዕዝ ቁጥሮችና የአረብኛ አቻቸው በአባሪነት ቀርቦበታል፡፡

በዋናነት የዚህ ጥናት ትኩረት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ ሲሆን በሁሉም ምዕራፎች ስር አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ የሚገኙበትን ገጽ በሚከተለው ሰንጠረዥ እንመለከታለን፡፡

**ሰንጠረዥ 1፡** በአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የሚገኙባቸው ገጾችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ምዕራፎች | የምዕራፉ ርዕስ | አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ያሉበት ገጽ |
|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | የሥራ ባህልና ምርት | ገጽ 7 እስከ 8 |
| ምዕራፍ ሁለት | የህይወት ክህሎቶች | ገጽ 21 |
| ምዕራፍ ሦስት | ሱስና አደንዛዥ ዕጽ | ገጽ 35 እስከ 36 |
| ምዕራፍ አራት | ልቦለድ | ገጽ 46 |
| ምዕራፍ አምስት | እንግዳ ተቀባይነት | ገጽ 55 እስከ 56 |
| ምዕራፍ ስድስት | ባህላዊ ክንውኖች | ገጽ 66 |
| ምዕራፍ ሰባት | አካቶ ትምህርት | ገጽ 76 |
| ምዕራፍ ስምንት | ሥነግጥም | ገጽ 85 እስከ 86 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ | አንድነትና ብዝሃነት | ገጽ 95 |
| ምዕራፍ አስር | ስደት | ገጽ 103 እስከ 104 |

#### 4.1.1.2. አዲሱ አስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ መርሀ ትምህርት አጭር መግለጫ

የአስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ መርሀ ትምህርት የተዘጋጀው በ2014 ዓ.ም በፌዴራል ደረጃ ሲሆን ይህ መርሀ ትምህርት በክፍል ደረጃው በተዘጋጀው የመምህሩ መምሪያ የመጨረሻዎቹ ገጾች ላይ ይገኛል፡፡ መርሀ ትምህርቱ በውስጡ በሁለቱ መንፈቅ የተከፋፈለ በየምዕራፉ የተሸነሸነ የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ አጠቃላይ ዓላማዎች (የሚጠበቁ ውጤቶች)፣ የቋንቋ ማስተማሪያ አዉደ ርዕስ፣ ከተማሪዎች የሚጠበቅ የክሂሎት ብቃት፣ ይዘት፣ የመማር ስልቶችና የመርጃ መሳሪያዎች እና የምዘና ዘዴዎችን አካትቶ ይዟል፡፡

የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት በመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት በአምስት ምዕራፎች ስር 48 (አርባ ስምንት) አጠቃላይ ዓላማዎችን፣ በሁለተኛ መንፈቀ ዓመት በአምስት ምዕራፎች ስር 49 (አርባ ዘጠኝ) አጠቃላይ ዓላማዎችን፣ በድምሩ በዓመቱ 97 (ዘጠና ሰባት) አጠቃላይ ዓላማዎችን አጠቃልሎ የያዘ ነው፡፡

እንደ አጠቃላይ የዚህ ጥናት ትኩረት አዲስ በተዘጋጀው የአስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ በመሆኑ መልመጃዎቹ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸው ግንኙነት በሚቀጥሉት ክፍሎች ተተንትኖ ቀርቧል።

#### 4.1.2. በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አቀራረብ ትንተና

በመማሪያ መጽሐፉ በሁሉም ምዕራፎችና ማስተማሪያ ርዕሶች ስር የንባብ መልመጃዎች በቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜ እና በድህረ ንባብ (አንብቦ የመረዳት) ተግባራት ተከፋፍለው ቀርበዋል። ነገር ግን በዚህ ጥናት ለትንተና የቀረበው አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለው ተጣጥሞሽ በመሆኑ ትኩረቱ በአንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ላይ ብቻ ይሆናል።

**ሰንጠረዥ 2፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አጠቃላይ መግለጫ**

| ምዕራፍ | በየምዕራፉ የትም/ቱ ርዕስ | ለማስተማሪያ የቀረበ ምንባብ | ትዕዛዝ | ዝርዝር መልመጃዎች/ተግባራት |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | የሥራ ባህልና ምርት | አውራምባ | አንድ | የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት በጽሑፍ መልሱ። |
| | | | ሁለት | ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን አማራጭ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ። |
| | | | ሦስት | የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ። |
| ምዕራፍ ሁለት | የህይወት ክህሎቶች | ቴክኖሎጂ | አንድ | የምንባቡን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች በጥሞና ከአነባባችሁ በኋላ ትክክል የሆኑትን "እውነት"፣ ትክክል ያልሆኑትን "ሀሰት" በማለት መልሱ። |
| | | | ሁለት | የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ። |
| | | | ሦስት | የጽሑፍን ፍሬ ሀሳብ በአንድ አንቀጽ ጻፉ። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ ሦስት | ሉስና አደንዛዥ ዕጽ | ሉስና ማገገሚያ መንገዶቹ | አንድ | ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆኑትን "እውነት"፣ ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ:: |
| | | | ሁለት | ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን አማራጭ ምረጡ:: |
| | | | ሦስት | ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በትእዛዛቱ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ:: |
| | | | አራት | ሉስ በኢትዮጵያ ትምህርትና ምጣኔ ሀብት ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖዎች ከተለያዩ ሰነዶች (ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች፣ ከድረ ገጽና ከመሰሳሉት) በማንበብ በማስታወሻዎቻችሁ ላይ ከአሰፈራችሁ በኋላ መረጃዎቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ:: |
| ምዕራፍ አራት | ልቦለድ | ሽክም | አንድ | በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ ስጡ:: |
| | | | ሁለት | ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለጥያቄዎቹ ተስማሚውን መልስ ስጡ:: |
| | | | ሦስት | መምህራችሁ የልቦለድ ንባብ መከታተያ ጽሑፍ አዘጋጅተው ይሰጧችኋል:: እናንተም በተሰጣችሁ የንባብ መከታተያ መሰረት መጽሐፉን አንብባችሁ ስትጨርሱ የንባብ መከታተያውን ጥያቄ ሰርታችሁ ለመምህራችሁ ትመልሳላችሁ :: |
| ምዕራፍ አምስት | እንግዳ ተቀባይነት | እንግዳ ተቀባይንት | አንድ | በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ ስጡ:: |
| | | | ሁለት | ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎቹ ተስማሚውን መልስ ምረጡ:: |
| | | | ሦስት | ከላይ የቀረበውንና ስለእንግዳ ተቀባይነት የቀረበውን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ምንባብ በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ስለእንግዳ አቀባበል ባህላችን በክፍል ውስጥ ሚና ወስዳችሁ (እንግዳና እንግዳ ተቀባይ በመሆን) ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡት፡፡ |
| ምዕራፍ ስድስት | ባህላዊ ክንውኖች | ሀገረሰባዊ የሕክምና ጥበብ | አንድ | ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በጥሞና በማንበብ ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡ |
| | | | ሁለት | የሚከተሉትን ተግባራት በትእዛዛቱ መሠረት ፈጽሙ፡፡ |
| ምዕራፍ ሰባት | አካቶ ትምህርት | የአይበገሬነት ተምሳሌት | አንድ | ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ፡፡ |
| | | | ሁለት | የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ከአነበባችሁ በኋላ በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆነውን "እውነት"፣ ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡ መልሳችሁ ሀሰት ከሆነ ምክንያታችሁንም በአጭሩ ግለጹ፡፡ |
| ምዕራፍ ስምንት | ሥነግጥም | ኢትዮጵያዊ ነን!! | አንድ | ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለጥያቄዎቹ ተስማሚውን መልስ ስጡ፡፡ |
| | | | ሁለት | ከላይ የተገለጸውን የግጥም ባህሪይ ካነበባችሁ በኋላ ከላይ ያነበባችሁት ግጥም በየትኛው የግጥም ባህሪ የተጻፈ ነው? አጭር መልስ ጻፉ፡፡ |
| | | | ሦስት | የሚከተለውን ግጥም በቃላችሁ ያዙና ክፍል ውስጥ በተራ አንብቡት፡፡ |
| ምዕራፍ ዘጠኝ | አንድነትና ብዝሃነት | የተፈጥሮ መንታ ገፅታዎች | አንድ | በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡ |
| | | | ሁለት | ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለጥያቄዎቹ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ተስማሚውን መልስ ምረጡ። |
| ምዕራፍ አስር | ስደት | ስደት | አንድ | በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ ስጡ። |
| | | | ሁለት | ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ለጥያቄዎቹ ተስማሚውን መልስ ምረጡ። |

በሰንጠረዥ ሁለት እንደቀረበው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባሉ ዘጠኝ ምዕራፎች ስር በጠቅላላ 27 (ሃያ ሰባት) የተለያዩ መልመጃዎች በምዕራፍ አንድ ሥር ሶስት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች፣ በምዕራፍ ሁለት ስር ሦስት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች፣ በምዕራፍ ሶስት ስር አራት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች፣ በምዕራፍ አራት ስር ሶስት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች፣ በምዕራፍ አምስት ስር ሶስት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች፣ በምዕራፍ ስድስት ስር ሁለት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች፣ በምዕራፍ ሰባት ስር ሁለት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች፣ በምዕራፍ ስምንት ስር ሶስት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች፣ በምዕራፍ ዘጠኝ ስር ሁለት፣ እንዲሁም በምዕራፍ አስር ስር ሁለት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የቀረቡ ሲሆን ሁሉም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር ዓላማ ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያካተቱ መሆናቸውን በሰነድ ፍተሻው የተገኘ መረጃ ያሳያል።

**ሰንጠረዥ 3፡ በአስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር በቀረቡ መልመጃ ጥያቄዎች ዝርዝር መግለጫ**

| ምዕራፍ | ጠቅላላ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ብዛት | አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃ ጥያቄ ዓይነቶች | | | | በየምዕራፉ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ ጥያቄዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክፍት ጥያቄዎች | ዝግ ጥያቄዎች | | | |
| | | | እውነት/ሀሰት | አዛምድ | ምርጫ | |
| ምዕራፍ አንድ | 3 | 5 | 5 | - | 5 | 15 |
| ምዕራፍ ሁለት | 3 | 5 | 5 | - | - | 10 |
| ምዕራፍ ሶስት | 4 | 4 | 4 | - | 5 | 13 |
| ምዕራፍ አራት | 3 | 1 | 5 | - | 5 | 11 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አምስት | 3 | 1 | 6 | - | 8 | 15 |
| ምዕራፍ ስድስት | 2 | 6 | 6 | - | - | 12 |
| ምዕራፍ ሰባት | 2 | 6 | 6 | - | - | 12 |
| ምዕራፍ ስምንት | 3 | 2 | - | - | 5 | 7 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ | 2 | - | 8 | - | 6 | 14 |
| ምዕራፍ አስር | 2 | - | 8 | - | 5 | 13 |
| ድምር | 27 | 30 | 53 | - | 39 | 122 |
| በፐርሰንት (በ%) | | 24.6% | 43.4% | - | 32% | 100% |

በሰንጠረዥ ሦስት እንደተብራራው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ ጠቅላላ መልመጃዎች ብዛት 27 (ሃያ ሰባት) ሲሆን እያንዳንዳቸው መልመጃዎች በየምዕራፎቹ ስር በተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል፡፡

በተለያዩ ትዕዛዞች ተዘጋጅተው የቀረቡ አጠቃላይ ጥያቄዎች ብዛት 122 (አንድ መቶ ሃያ ሁለት) ሲሆን 30 (ሰላሳ) ክፍት ጥያቄዎች በፐርሰንት 24.6%፣ 92 (ዘጠና ሁለት) ዝግ ጥያቄዎች በፐርሰንት 75.4% ናቸው፡፡ በዝግ የቀረቡ ጥያቄዎች እውነት/ሀሰት ጥያቄዎች 53 በፐርሰንት 43.4%፣ እንዲሁም የምርጫ ጥያቄዎች 39 በፐርሰንት 32% በመሆን በየምዕራፍ ተሸንሽነው መቅረባቸውን በሰነድ ፍተሻው የተገኘ መረጃ ያመለክታል፡፡

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አብዛኞች ጥያቄዎች በዝግ መልክ የቀረቡ ሲሆን በአዛምድ መልክ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ ጥያቄዎች ያለመኖራቸውን ነው፡፡

በሌላ መልክ ከቀረቡት አጠቃላይ መልመጃዎች 43.4 በመቶ የእውነት/ሀሰት ጥያቄ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡ ይህም ካሉት ሌሎች መልመጃዎች ከፍተኛ ቁጥር ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡- ስሰነድ ፍተሻው የተዘጋጁ መስኪያዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ስሳሳቸው ተጣጥሞሽ የሚያሳይ መረጃ**

| ምዕራፍ | የመልመጃዎች ብዛት | ተገቢ የትምህርት ገለጻ በቅድሚያ ስለመደረጉ | | ተገቢ ዒላማ ስለመነደፉ | | ተማሪዎች የሚሰሩት ተግባራት ስለመቀረባቸው | | የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ስለመካተቱ | | የጊዜ መርሀ ግብር ተሸንሽኖ ስለመቀረቡ | | የምዘና ስልት ስለመካተቱ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚገናኙ | የማይገናኙ | የሚገናኙ | የማይገናኙ | የሚገናኙ | የማይገናኙ | የሚገናኙ | የማይገናኙ | የሚገናኙ | የማይገናኙ | የሚገናኙ | የማይገናኙ |
| አንድ | 3 | 3 | - | 3 | - | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| ሁለት | 3 | 3 | - | 3 | - | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| ሦስት | 4 | 4 | - | 4 | - | 4 | - | 4 | - | - | 4 | 4 | - |
| አራት | 3 | 3 | - | 3 | - | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| አምስት | 3 | 3 | - | - | 3 | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| ስድስት | 2 | 2 | - | 2 | - | 2 | - | 2 | - | - | 2 | 2 | - |
| ሰባት | 2 | 2 | - | - | 2 | 2 | - | 2 | - | - | 2 | 2 | - |
| ስምንት | 3 | 3 | - | 3 | - | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| ዘጠኝ | 2 | 2 | - | 2 | - | 2 | - | 2 | - | - | 2 | 2 | - |
| አስር | 2 | 2 | - | 2 | - | 2 | - | 2 | - | - | 2 | 2 | - |
| ድምር | 27 | 27 | - | 22 | 5 | 27 | - | 27 | - | - | 27 | 27 | - |
| በመቶኛ | 100% | 100% | 0 | 81.5% | 18.5% | 100% | 0 | 100% | 0 | 0 | 100% | 100% | 0 |

በሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው 27 (ሃያ ሰባት) አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ አጠቃላይ መልመጃዎች ተገቢ የትምህርት ገለጻ የተሰጣቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት 27 (ሃያ ሰባት) መልመጃዎች

በሙሉ ተገቢ ገለጻ ከተሰጠ በኂላ የቀረቡና ለማስተማሪያ ከቀረበው ምንባብ (ማብራሪያ) ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ (100%) ይሆናል፡፡

የተማሪዎችን ብቃት ለመለካት የሚያስችል ተገቢ ዓላማ ከመነደፉ ጋር በተያያዘ ካሉት አስር ምዕራፎች መካከል በምዕራፍ አምስትና በምዕራፍ ሰባት የቀረቡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችን በሚመለከት በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተነደፈ ዓላማ የሌለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ ከቀረቡት መልመጃዎች በመቶኛ (81.5%) የተነደፈላቸው ሲሆን (18.5%) ተገቢ ዓላማ ያልተነደፈላቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሶስተኛ መለኪያ ተማሪዎች የሚሠሩት ተግባራት ተዘጋጅተው ስለመቅረባቸው የሚገልጽ ሲሆን በሁሉም ምዕራፎች በሃያ ሰባት መልመጃዎች ስር ተማሪዎችን የሚያሳትፉ የተለያዩ ተግባራት ተዘጋጅተው መቅረባቸውን የሰነድ ፍተሻው ያሳያል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 100% ይሆናል፡፡

አራተኛው መለኪያ ስለማስተማሪያ ስነዘዴ የቀረበ ሲሆን መማሪያ መጽሐፉ ባሉት አስር ምዕራፎች ስር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የተዘጋጁ ሃያ ሰባት መልመጃዎች የተለያዩ የማስተማሪያ ስነ ዘዴዎችን ታሳቢ አድርገው የተዘጋጁ መሆናቸውን ከሰነድ ፍተሻው የተገኘ መረጃ የሚያሳይ ሲሆን ይህም ከመርሀ ትምህርቱ ጋር 100% ግንኙነት ያለው ይሆናል፡፡

በሰነድ ፍተሻው ከተገኘ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የጊዜ መርሀ ግብር በመምህሩ መምሪያ ላይ በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ላይ በየምዕራፎች ተሸንሽኖ የቀረበ ሲሆን በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ግን ተሸንሽኖ አልቀረበም፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ሙሉ በሙሉ (100%) የማይገናኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከሰነድ ፍተሻው የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር የተገናዘቡና የተማሪዎችን የመረዳት ችሎታቸውን ሊለኩ የሚችሉ ተገቢ የምዘና ስልቶች ተካትተው ተገኝተዋል፡፡ ይህም የመማሪያ መጽሐፉንና የመርሀ ትምህርቱን ግንኙነት 100% ያደረገዋል፡፡

በሌላ መልኩ መማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃ ጥያቄዎች በብዛት ተማሪዎች በግል እንዲሠሩ የሚጋብዙ እንጂ በቡድን እንዲሠሩ የሚጋብዙ እንዳልሆኑ በሰነድ

ፍተሻ የተገኘ መረጃ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም አብዛኞች መልመጃዎች ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ የሚያዙ መሆናቸውን መረጃው አመላክቷል፡፡

በጠቅለላ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የመርሀ ትምህርቱ እና የመማሪያ መጽሀፉ ግንኙነት በንጽጽር (Ratio) (80.25 ፡ 19.75) ወይም 80.25 % ተጣጥሞሽ ያለው ሲሆን 19.75% የማይጣጣም ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 4.1.3. በቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

**ሰንጠረዥ 5፡- ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን ዳራዊ መረጃ**

| የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ | ጾታ | ዕድሜ | የአገልግሎት ዘመን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በሴርተፊኬት | በዲፕሎማ | በድግሪ | ድምር |
| አማርኛ | ሴት | 34 | - | 7 | 5 | 12 |
| አማርኛ | ወንድ | 37 | 5 | 8 | 4 | 17 |
| አማርኛ | ወንድ | 28 | - | - | 7 | 7 |

በሰንጠረዥ አራት የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው ለቃለ መጠይቁ የተመረጡ መምህራን ሦስት ሲሆኑ ሦስቱም መምህራን የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ አማርኛ ነው፡፡ ሴት የአማርኛ መምህርት የአገልግሎት ዘመኗ አስራ ሁለት (በዲፕሎማ ሰባት፣ በድግሪ አምስት) ሲሆን የመጀመሪያው ወንድ የአማርኛ መምህር ደግሞ በሴርተፊኬት አምስት፣ በዲፕሎማ ስምንት፣ እንዲሁም በድግሪ አራት በድምሩ አስራ ሰባት ዓመታትን ያገለገለ እንደሆነና ሁለተኛው ወንድ የአማርኛ መምህር ሰባቱንም ዓመታት በድግሪ ያገለገሉ መሆናቸውን መረጃው ያስረዳል፡፡ ስለሆነም ተተኳሪ መምህራን ቀደም ሲል የነበረውን መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፉን ከአዲሱ እያነጻጸሩ ተገቢና ተዓማኒ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ይገመታል፡፡

ከሰነድ ፍተሻው በመቀጠል ተተኳሪ መጽሐፍን ተጠቅመው እያስተማሩ ካሉ መምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ቃለ መጠይቁ በሁለት መመሪያዎች የተዘጋጀ ሲሆን የመጀመሪያው መመሪያ በክፍት መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሆኖ ሁለተኛው መመሪያ ደግሞ በዝግ ወይም በምርጫ መልክ ቀርቧል፡፡

## ሀ. በክፍት አጠያየቅ የቀረቡ ቃለ መጠይቆች ትንተና፤

በክፍል አንድ የቀረቡ ቃለ መጠይቆች ብዛታቸው አስር ሲሆን ሦስቱ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡- ለክፍል አንድ ቃለ መጠይቅ መምህራን የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ መረጃ**

| ተ/ቁ | ቃለ መጠይቆች | መምህር 1 | መምህር 2 | መምህር 3 | ውጤት በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አዎ | አይደለም |
| 1 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ ግቦችን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው? | አዎ | አዎ | አዎ | 100 | 0 |
| 2 | በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ሁሉንም የመልመጃ ዓይነት አካትተው የያዙ ናቸው? | አይደለም | አዎ | አዎ | 66.7 | 33.3 |
| 3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የቀረቡት ተገቢ ገለጻ ከተሰጠ በኋላ ነው? | አዎ | አዎ | አይደለም | 66.7 | 33.3 |
| 4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ የመልመጃ ጥያቄዎች ሊይዟቸው የሚገባቸውን ባህሪያት የሚያሟሉ ናቸው? | አዎ | አይደለም | አዎ | 66.7 | 33.3 |
| 5 | በየክፍለ ጊዜው የተሸነሸኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ጋር የተጣጣሙ ናቸው? ካልሆነስ እንዴት እየተገበሩት ነው? | አዎ | አይደለም | አይደለም | 33.3 | 66.7 |
| 6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በሁሉም ምዕራፎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የሚያስችሉ መልመጃዎች ተካተው ቀርበዋል? ጥያቄዎቹስ ከምንባቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ናቸው? | አዎ | አዎ | አዎ | 100 | 0 |
| 7 | የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለመገንባት የቃላት ትምህርትን ያካተቱ መልመጃዎች በየምንባቡ ስር ተደራጅተዋል? | አዎ | አዎ | አይደለም | 66.7 | 33.3 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መልመጃዎች የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ መገምገም የሚያስችሉ ናቸው? ሁሉንም ተማሪዎች ታሳቢ ያደረጉ ናቸው? | አይደለም | አዎ | አዎ | 66.7 | 33.3 |
| 9 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመርሀ ትምህርቱ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር የሚፈትሹ ናቸው? | አዎ | አዎ | አዎ | 100 | 0 |
| 10 | በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር የተገናዘቡ ናቸው ብለው ያምናሉ? ካልሆነስ ምን አስተያየት ይሰጣሉ? | አዎ | አዎ | አዎ | 100 | 0 |

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ ግቦችን ታሳቢ ያደረጉ መሆን ስላለመሆናቸው ለቀረበላቸው መጠይቅ ክፍሉን እያስተማሩ ያሉ ሶስቱም መምህራን "አዎ" የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን ይህም የሚያሳየው በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ ሁሉም (100%) መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ ግቦችን ታሳቢ ያደረጉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህን መረጃ ከሰነድ ፍተሻው ከተገኘ መረጃ ጋር ስንመለከት ተቃራራቢነት ያለው ይሆናል ማለት ነው፡፡

በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ሁሉንም የመልመጃ ዓይነት አካትተው የያዙ ስለሆናቸው ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ክፍሉን እያስተማሩ ካሉ መምህራን አንድ መምህር ሁሉንም የመልመጃ ዓይነት አካትቶ አልያዘም የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን ሁለቱ ደግሞ መልመጃዎቹ ሁሉንም የመልመጃ ዓይነት አካትተው ይዘዋል ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲታይ ከመልመጃዎቹ 66.7% ያህሉ ሁሉንም የመልመጃ ዓይነት አካትቶ የያዘ እንደሆነና አይደለም በሚል የተገኘ ውጤት 33.3% መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ተገቢ ገለጻ ከተሰጠ በኋላ መሆን አለመሆኑን ክፍሉን እያስተማሩ ላሉ ሦስት መምህራን መጠይቁ ቀርቦላቸው ሁለቱ መልመጃዎቹ የቀረቡት ተገቢ ገለጻ ከተደረገባቸው በኋላ

እንደሆነ ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንዱ መላሽ ግን አይደለም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከተተኳሪ መምህራን የተገኘ መረጃው እንደሚያመለክተው ከቀረቡት አጠቃላይ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች 66.7% ያህሉ ተገቢ ገለጻ ተሰጥቶበት የተዘጋጀ መሆኑንና 33.3% ደግሞ ገለጻ ያልተደረገበት መሆኑን ማወቅ ተችሏል፡፡ በሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መረጃ ጋር ስናነጻጽር በሁለቱም የተገኙ መረጃዎች ተቀራራቢነት ያላቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ የመልመጃ ጥያቄዎች ሊይዟቸው የሚገባቸውን ባህሪያት የሚያሟሉ ስለመሆናቸው መጠይቅ ከተደረገላቸው መምህራን መካከል ሁለቱ መላሾች አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ የመልመጃ ጥያቄዎች ሊይዟቸው የሚገባቸውን ባህሪያት አሟልተው የቀረቡ ስለመሆናቸው ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንድ መላሽ ግን ባህሪያቱን ያላሟሉ እንዳልሆኑ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህንን ምላሽ በመቶኛ ስንመለከት ከቀረቡት መልመጃዎች 66.7% ያህሉ አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ የመልመጃ ጥያቄዎች ሊይዟቸው የሚገባቸውን ባህሪያት አሟልተው የተዘጋጁ ሲሆን 33.3% ያላሟሉ ናቸው ማለት ነው፡፡

በየክፍለ ጊዜው የተሸነሸኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ጋር የተጣጣሙ መሆን ስላለመሆናቸውና ካልሆነስ እንዴት እየተገበሩት እንዳለ እንዲገልጹ መጠይቅ ከቀረበላቸው ሦስት መምህራን መካከል ሁለቱ መላሾች የተጣጣሙ አለመሆናቸውንና የጊዜ መርሀ ግብር በመርሀ ትምህርቱ ብቻ የተሸነሸነ እንደሆነና በመማሪያ መጽሐፉ እንዳልቀረበ እንዲሁም የጊዜ መርሀ ግብር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባለመቅረቡ የራሳቸውን የጊዜ ዕቅድ ብቻ አዘጋጅተው እንደሚተገብሩት የመለሱ ሲሆን አንዱ መላሽ ደግሞ በየክፍለ ጊዜው የተሸነሸኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ጋር የተጣጣሙ ናቸው ሲሉ ምላሽ ሰጥዋል፡፡ ከመላሾቹ የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው ከአጠቃላይ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች 33.3% ያህሉ ብቻ በመርሀ ትምህርቱ ተሸንሽነው ከተቀመጡ የጊዜ መርሀ ግብር ጋር የተጣጣሙና 66.7% ደግሞ ያልተጣጣሙ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ይህም በሰነድ ፍተሻው ከተገኘው መረጃ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ያደርገዋል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በሁሉም ምዕራፎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የሚያስችሉ መልመጃዎች ተካተው ስለመቅረባቸውና ጥያቄዎቹም ከምንባቡ ጋር ቀጥተኛ

ግንኙነት ያላቸው መሆን ስላለመሆናቸው መጠይቅ ከቀረበላቸው ክፍሉን ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ሁሉም (100%) መላሾች የተዘጋጁት ሁሉም መልመጃዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የሚያስችሉ መልመጃዎች ስለመሆናቸውና ጥያቄዎቹም ከምንባቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ምላሽ ሰጥዋል፡፡ ይህም መርሀ ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ያስረዳል፡፡

የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለመገንባት የቃላት ትምህርትን ያካተቱ መልመጃዎች በየምንባቡ ስር ስለመደራጀታቸው መጠይቁ ክፍሉን እያስተማሩ ላሉ መምህራን ሁሉም መምህራን የቀረበ ሲሆን ሁለት መላሾች የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለመገንባት የቃላት ትምህርትን ያካተቱ መልመጃዎች በየምንባቡ ስር የተደራጁ ስለመሆናቸው ምላሽ ሲሰጡ አንዱ መላሽ ደግሞ የቃላት ትምህርትን ያካተቱ መልመጃዎች በየምንባቡ ስር ያልተደራጁ ስለመሆናቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህንን በመቶኛ ስናሰላ ከአጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መልመጃዎች 66.7% ያህል የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለመገንባት የቃላት ትምህርትን ያካተቱ መልመጃዎች በየምንባቡ ስር የተደራጁ መሆናቸውንና 33.3% ያላካተተ መሆኑን መረጃው አመላክቷል፡፡

የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መልመጃዎች የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ መገምገም የሚያስችሉ መሆን ስላለመሆናቸውና ሁሉንም ተማሪዎች ታሳቢ ያደረጉ ናቸው ወይስ አይደሉም በሚል ለቀረበው መጠይቅ መጠይቁን ከመለሱት ሶስት መላሾች ሁለቱ የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ መገምገም የሚያስችሉ መልመጃዎች ስለመደራጀታቸውና ሁሉንም ተማሪዎች ታሳቢ ያደረጉ ስለመሆናቸው ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንዱ መላሽ የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ መገምገም የሚያስችሉ እንዳልሆኑና ሁሉንም ተማሪዎች ታሳቢ ታሳቢ ያላደረጉ እንደሆኑ ምላሽ ሰጥዋል፡፡ ይህንንም ስንመለከት 66.7% ያህል መልመጃዎች የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ መገምገም የሚያስችሉና ሁሉንም ተማሪዎች ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውንና 33.3% መልመጃዎች የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ መገምገም የማያስችሉና ሁሉንም ተማሪዎች ታሳቢ ያላደረጉ መሆናቸውን መረጃው አሳይቷል ማለት ነው፡፡

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመርሀ ትምህርቱ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር የሚፈትሹ መሆን ስላለመሆናቸው መጠይቅ የተደረገላቸው ሁሉም (100%) መላሾች ሁሉም መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመርሀ ትምህርቱ ከተቀመጡ ግቦች

አንጻር የሚፈትሹ ስለመሆናቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመርሀ ትምህርቱ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር 100% የሚፈትሹ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር የተገናዘቡ ስለመሆናቸው መጠይቅ የቀረበላቸው ክፍሉን እያስተማሩ ያሉ ሁሉም (100%) መምህራን መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር የተገናዘቡ እንደሆኑ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ይህም በሰነድ ፍተሻው ከተገኘው መረጃ ጋር ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

### ለ. በዝግ (በምርጫ) የቀረቡ ቃለ መጠይቆች ትንተና፤

**ሰንጠረዥ 7፡- ከክፍል ሁለት ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ**

| ተ/ቁ | ቃለ መጠይቆች | አማራጮች | መምህር 1 | መምህር 2 | መምህር 3 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ዝግጅትና የይዘት አቀራረብ ለክፍል ደረጃው ያላቸው ተስማሚነት ምን ያህል ነው? | ሀ) በጣም ከፍተኛ<br>ለ) ከፍተኛ<br>ሐ) መካከለኛ<br>መ) ዝቅተኛ | ሐ) መካከለኛ | ለ) ከፍተኛ | ለ) ከፍተኛ |
| 2 | መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች መመሪያዎች ግልጽነት ምን ያህል ነው? | ሀ) በጣም ከፍተኛ<br>ለ) ከፍተኛ<br>ሐ) መካከለኛ<br>መ) ዝቅተኛ | ለ) ከፍተኛ | ሀ) በጣም ከፍተኛ | ለ) ከፍተኛ |
| 3 | የቀረቡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የማጠቃለል ችሎታ ለማሳደግ ምን ያህል ያስችላሉ? | ሀ) በጣም ከፍተኛ<br>ለ) ከፍተኛ<br>ሐ) መካከለኛ<br>መ) ዝቅተኛ | ሀ) በጣም ከፍተኛ | ሀ) በጣም ከፍተኛ | ሀ) በጣም ከፍተኛ |
| 4 | መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን የቃላት ሀብት እድገትን ለማሻሻል ምን ያህል ያተኮሩ ናቸው ብለው ያስባሉ? | ሀ) በጣም ከፍተኛ<br>ለ) ከፍተኛ<br>ሐ) መካከለኛ<br>መ) ዝቅተኛ | ሐ) መካከለኛ | ለ) ከፍተኛ | ሐ) መካከለኛ |

በክፍል ሁለት በምርጫ የቀረቡ ቃለ መጠይቆች ብዛት አራት ሲሆን ክፍሉን እያስተማሩ ካሉ መምህራን የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ዝግጅትና የይዘት አቀራረብ ለክፍል ደረጃው ያላቸው ተስማሚነት ምን ያህል ነው? በሚል ለቀረበው የምርጫ ቃለ መጠይቅ በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የሚሉ አራት አማራጮች የቀረቡ ሲሆን ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ሶስት መምህራን መካከል ሁለቱ ከፍተኛ የሚል አማራጭ የመረጡ ሲሆን አንድ መላሽ መካከለኛ የሚል አማራጭ መርጧል፡፡ ስለሆነም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ዝግጅትና የይዘት አቀራረብ ለክፍል ደረጃው ተስማሚነት ባለው መንገድ የተዘጋጀ ሆኖ ተገኝቷል ማለት ነው፡፡ ይህም ሀሳብ ከፍ ሲል በመመሪያ አንድ ተተንትኖ ከቀረበው መረጃ ጋር ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች መመሪያዎች ግልጽነት ምን ያህል ነው? በሚል ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የሚሉ አራት አማራጮች የቀረቡ ሲሆን ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ሶስት መምህራን ሁለቱ ከፍተኛ የሚል አማራጭ የመረጡ ሲሆን አንድ መላሽ በጣም ከፍተኛ የሚል ምላሽ መርጧል፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የቀረቡ መመሪያዎች ግልጽነት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

የቀረቡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የማጠቃለል ችሎታ ለማሳደግ ምን ያህል ያስችላሉ? በሚል ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የሚሉ አራት አማራጮች የቀረቡ ሲሆን አራቱም መላሾች በጣም ከፍተኛ በሚል መልመጃዎቹ የተማሪዎችን የማጠቃለል ችሎታ ለማሳደግ የሚያስችሉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህም በመመሪያ አንድ ከቀረበው መረጃ ጋር ተመሳሳይነት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ስለሆነም በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች የተማሪዎችን የማጠቃለል ችሎታ ለማሳደግ የሚያስችሉ ናቸው ማለት ነው፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ መልመጃዎች የተማሪዎቹን የቃላት ሀብት እድገትን ለማሻሻል ምን ያህል ያተኮሩ ናቸው ብለው ያስባሉ? በሚል ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የሚሉ አራት አማራጮች ያሉት ሲሆን ከመላሾቹ መካከል ሁለቱ

መካከለኛ የሚል አማራጭን የመረጠ ሲሆን አንዱ ከፍተኛ የሚል አማራጭን መርጧል፡፡ ይህም በመመሪያ አንድ ተተንትኖ ከቀረበው መረጃ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ መልመጃዎች የተማሪዎችን የቃላት ሀብት ዕድገትን ለማሻሻል ትኩረት ያደረጉ መሆናቸውን መረጃው አመላክቷል ማለት ነው፡፡

የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን እየተገበሩ ካሉ መምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በንጽጽር (Ratio) (76.7 ፡ 23.3) ወይም 76.7% መማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ምሉዕነት ያላቸው (ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ተጣጥሞሽ ያላቸው) ሲሆኑ 23.3% የሚሆኑት ደግሞ ጉድለት የሚታይባቸው (ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ተጣጥሞሽ የሌላቸው) ናቸው ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻው እና ከቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የአዲሱ አስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ እና መርሀ ትምህርቱ ያለው ተጣጥሞሽ በንጽጽር (Ratio) (78.5 ፡ 21.5) ወይም 78.5% ተጣጥሞሽ ያላቸው ሲሆን 21.5% ደግሞ ተጣጥሞሽ የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል ማለት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር የተሻለ ተጣጥሞሽ ያላቸው መመሆኑን ያሳያል ማለት ነው፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የነበረው አዲስ በተዘጋጀው የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ ሲሆን ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሰነድ ፍተሻ እና ከቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው የተገኙት መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

በትንተናው የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የመርሀ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፉ ተጣጥሞሽ በንጽጽር (Ratio) (78.5 ፡ 21.5) መሆኑን በጥናቱ የተገኘው ውጤት አመላክቷል፡፡ ይህም በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት አበበ እና ሌሎች (2008)፣ እንዲሁም ይመኙሻል (2014) ባደረጉት ጥናት በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ መካከል ያለው ተዛምዶ ጥሩ እንደሆነ ከገለጹት ሀሳብ ጋር ይገናኛል ማለት ነው፡፡

መጽሐፉን እየተገበሩ ላሉ መምህራን በቃለ መጠይቅ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ግልጽ መመሪያ ስለመኖራቸው ለተነሳው ሀሳብ የተገኘው ውጤት

መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ቀረቡ መልመጃዎች ግልጽ መመሪያ እንደተዘጋጀላቸው ያሳያል፡፡ ይህም ይመኙሻል (2014) ባደረጉት ጥናት ከተገኘው ውጤት ጋር ተመሳሳይ ሆኗል፡፡

በሰነድ ፍተሻው በተገኘው መረጃ የመርሀ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሀፉ ተጣጥሞሽ የተሻለ መሆኑን ውጤቱ ያመለክታል፡፡ ይህም በክለሳ ድርሳናት 2.1.6 ላይ Tufts (2013) ያብራሩትን የመርሀ ትምህርት አላባውያንን በተመለከተ ከተዘረዘረው ሀሳብ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡

በመረጃ ትንተናው የተገኘው ውጤት መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች ሁሉንም የመልመጃ ዓይነት ያካተቱ መመሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም በክለሳ ድርሳናት 2.1.7.1 ላይ Rivers (1981፣ 387) እና ሌሎች ካብራራቱ ሀሳብ ጋር የሚገናኝ ነው፡፡

በተመሳሳይ በመረጃ ትንተናው የተገኘ ውጤት እንደሚያሳየው የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች በክለሳ ድርሳናት 2.1.7.1 ላይ Nuttal (1982፣132) አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ የመልመጃ ጥያቄዎች ሊይዟቸው የሚገባ ባህሪያት ብለው ካብራሩት ሀሳብ ጋር ግንኙነት ያለው ነው፡፡

በመረጃ ትንተና የተገለጸው ሀሳብ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የቀረቡት ተገቢ ገለጻ ከተሰጠ በኋላ ስለመሆኑ ይገልጻል፡፡ ይህም Tufts (2013) ካብራሩት የመረሀ ትምህርት አላባውያን አንጻር ተዛምዶ ያለ መሆኑን አሳይቷል ማለት ነው፡፡

በሰነድ ፍተሻው እና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በየክፍለ ጊዜው የተሸነሸኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ጋር የተጣጣሙ ያለ መሆናቸውን እንዲሁም ክፍለ ጊዜ በመርሀ ትምህርቱ ተሸንሽኖ ቀርቦ በመማሪያ መጽሐፉ ያልቀረበ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም Tufts (2013) ካብራሩት ከመርሀ ትምህርት አላባውያን ሀሳብ ጋር የሚቃረን ይሆናል ማለት ነው፡፡

በክለሳ ድርሳናት 2.1.7.1. ላይ Nuttal (1982፣133) የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነት በሚል ርዕስ የአዛምድ ጥያቄዎች የሚካተቱ መሆናቸውን ቢያብራም በዚህ መማሪያ መጽሐፍ በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ውስጥ አንድም የምርጫ ጥያቄ ያልተካተተ መሆኑን በሰነድ ፍተሻው የተገኘ መረጃ አመላክቷል፡፡ ይህም ከምሁሩ ሀሳብ ጋር የሚቃረነረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ መልክ ከቀረቡት አጠቃላይ መልመጃዎች 43.4 በመቶ የእውነት/ሀሰት ጥያቄ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡ ይህም Nuttal (1982፣133) "በእውነት/ሀሰት ጥያቄዎች ተማሪዎች መልስ የማግኘትና የማጣት ዕድላቸው ሀምሳ ሀምሳ ነው፡፡" ሲሉ ከገለጹት ሀሳብ አንጻር የተማሪዎችን በሰፊው የመመራመርን ዕድል የሚገታ ይሆናል፡፡

እንደ አጠቃላይ በዚህ ጥናት የተዳሰሰው የመርሀ ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፉ ተጣጥሞሽ አብዛኛው በጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ሲሆን መጠነኛ ክፍተቶች ያሉት መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዋና ዓላማ አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ ማድረግ ነበር። ይህንን ዓላማ ለማሳካት በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍ ተግባራዊ ሆኗል።

በተደረገው ትንተና የመማሪያ መጽሐፉና የመርሀ ትምህርት ተጣጥሞሽ ተፈትሾ የቀረበ ሲሆን ተዛምዷቸው በንጽጽር (Ratio) (78.5 ፡ 21.5) ነው። ይህም መርሀ ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ የተሻለ ተጣጥሞሽ እንዳለው የሚያሳይ መሆኑ ተመላክቷል።

በሌላ መልኩ የማስተማሪያ ክፍለ ጊዜ ወይም የጊዜ መርሀ ግብር በመርሀ ትምህርት ተሸንሽኖ የቀረበ ሲሆን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያልቀረበ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ተገቢ የትምህርት ገለጻ ከተደረገ በኋላ መሆኑን ውጤቱ አሳይቷል።

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ ግቦችን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

በአስረኛ ክፍል አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ሌሎችን የመልመጃ ዓይነቶች አካትተው የያዙ ምንም ዓይነት የአዛምድ መልመጃዎችን ያላካተተ መሆኑን በሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ አመለካቷል።

በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መልመጃዎች የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ መገምገም የሚያስችሉ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

እንደ አጠቃላይ አዲስ የተዘጋጀው የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ የቀረቡ ግቦችን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን የተገኘው ውጤት ያመለክታል ማለት ነው፡፡

## 5.2. አስተያየት

ጥናቱ ከፍ ሲል በቀረበው መልክ ማጠቃለያ የተሰጠው ሲሆን አጥኚዋ የታዘበችውን አስተያየት ለሚመለከታቸው አካላት እንደሚከተለው ሰጥታለች፡፡

ለመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች በመጽሐፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች ከቀረቡት መመሪያዎች መካከል የመለማመጃ ጥያቄዎቹ በምን መልኩ እንደሚተገበሩ የተሟላ መረጃ በሚሰጡ መልክ የተካተቱ ቢሆንም የተወሰኑት ደግሞ ስለመልመጃዎቹ አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ ለአብነትም "የሚከተሉትን በቃል መልሱ...፡፡" የሚሉ ትዕዛዛትን በሰፊው ያዘሉ ሲሆኑ ምላሻቸውም በግል ይሁን በቡድን ያልታወቁ መመሪያዎች በመጽሐፉ ውስጥ እንደሚገኙ በሰነድ ፍተሻው ማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሁሉም አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ምላሽ ስለሚሰጥባቸው በተሟላ ሁኔታ መመሪያዎች ቢዘጋጁ የተሻለ ነው፡፡

እንዲሁም የማስተማሪያ ክፍለ ጊዜ ወይም የጊዜ መርሀ ግብር በመርሀ ትምህርቱ ተሸንሽኖ የቀረበ ሲሆን በመማሪያ መጽሀፉ የቀረበ አለመሆኑን የትንተናው ውጤት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የመማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች የሚያዘጋጁትን የይዘት ስፋትን ታሳቢ ያደረገ የጊዜ መርሀ ግብር በመማሪያ መጽሐፉም  እንዲካተት ቢያደርጉ ተማሪዎች ይዘቱን መምህራቸውን ሳይጠብቁ የቱ ርዕስ ለመቼ እንደሚቀርብ ይረዳሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡

በተጨማሪ በክለሳ ድርሳናት 2.1.7.1. ላይ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አይነት በሚል ርዕስ የአዛምድ ጥያቄዎች የሚካተቱ መሆናቸውን ምሁራን ቢያስቀምጡም በዚህ መማሪያ መጽሐፍ በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ውስጥ አንድም የምርጫ ጥያቄ ያልተካተተ መሆኑን በሰነድ ፍተሻው የተገኘ መረጃ አመላክቷል፡፡ ስለሆነም የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች የአዛምድ ጥያቄዎችን ማካተት ቢችሉ የተሻለ ይሆናል፡፡

ከቀረቡት አጠቃላይ መልመጃዎች 43.4 በመቶ የሚሆነው የእውነት/ሀሰት መልመጃ መሆኑን በሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የመመራመርና በራሳቸው ችሎታ ሰፋ አድርገው የመሥራት እድልን የሚገድብ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡ ስለሆነም

የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች መማሪያ መጽሐፍ ሲያዘጋጁ ክፍት ጥያቄዎችን በሰፊው ማካተት ቢችሉ ተማሪዎችን በራሳቸው የመስራት ዕድል ያሰፋላቸዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ለጥናት አድራጊዎች ተመራማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ በስፋት ቢያጠኑ ለአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች፣ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሁም ለቋንቋው እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ እና የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ እንደሚያስችሉ አጥኝዋ ታምናለች፡፡ በመልመጃዎቹ ስር የሚካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ጽሑፉን ደጋግመው እንዲያነቡ የሚገፋፉ ሆነው ቢዘጋጁ ተመራጭነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የራሳቸውን የአነባበብ ስልት ተጠቅመው ምንባቡን የመረዳት፣ የመተርጎም፣ የማብራራት፣ የማጠቃለል እና ሌሎች ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት መንገድ የሚያሳይ በመሆኑ ነው፡፡

# ዋቢጽሑፎች


አበበ እና ሌሎቹ (2008) የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ከመማሪያ መጽሀፉና ከመርሃ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በወሎ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ያካሄዱት ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር:: (2014):: አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ የመምህር መምሪያ፣ አስረኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር:: (2014):: አማርኛ እንደፌዴራል ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣ አስረኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤

ያለው እንዳወቅ፡፡ (2009)፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ 3ኛ እትም፡፡

ይመኙሻል ቀለታ፡፡ (2014)፡፡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የይዘት አዘገጃጀትና አቀራረብ ፍተሻ (በ2007 ዓ.ም በታተመው የ5ኛ ክፍል እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድኅረ-ምረቃ መርሃ-ግብር በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነ-ዘዴ የአርቲስ ማስትሬት ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)፤

ግዛው (2008) በ2001 ዓ.ም የተዘጋጁት የ9ኛና የ10ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች በ2004ዓ.ም ከታተሙት የተማሪዉ መጻሕፍት ጋር ያላቸዉ የዓላማና የይዘት ተጣጥሞሽ በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል ለድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ያደረጉት ጥናት (ያልታተመ)፤

Ahmadi, M.R and Pourhosein, G.A. (2012).Reciprocal Teaching strategies and their impacts on English Reading Comprehension. Theory and Practice in language studies; 2 (10); 2053-2060

Barbara, N. (2004). Relating language teaching and content teaching. TESOL Quarterly, 13, 171.

Bintzi, W.P.1997.Exploring Reading night mares of middle and secondary school Teacher's, Journal of Adolescent and adult literarly 411, 23-24.

Carf Wenning. (2009). The syllabus as a tool for student-centered learning. Journal of General Education 50 (1), 56-74 Great Britain: long Dunn press.

Carrell, P.L. (2006). Can Reading Strategies be uccessfuly Taught? The Language Teacher Journal JALT.

Cilice Murcia. (1991). Teaching of Reading.

Cunningworth, A. (1989). Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials.Oxford: Oxford University Press.

David, A. (2005). Reading skills in English Delh: common welth publishers.

Dubin, F. and Olshtain, E. (1986).Course Design Developing Programs and Materials for Language Learning. Cambridge: Cambridge Universuty Press.

Feathers K.M. (2004). In for text : Reading and Learning. Toronto, Ontario;

Pippin publishin company.Cambridge, Cambridge university press.

Getachew Asirate. (1996). ‘’The Teaching of Reading in Government High Schools in Addis Ababa: a discrptive study.’’ Unpublished M.A Thesis, Addis Ababa University.

Greenwood, J.(1981). “Compression and Reading” in Abott, G. and Wingard, p.(ends) teaching of English as an International Language: A practical Guide. Oxford: Oxford University Press.

Grellet, F.(1981). Developing Reading Skills: A practical Guide to Reading Comphrensive Exercise. Cambridege: Cambridge University Press.

Hittleman, D.R. (1998).Developmental Reading,K-8 Teaching From a whole Language Perspective.(3Ed.), Columbus. Ohio; Merrill a Bell and Howell.

Hughes A. (1989). Testing for Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

Huthchison. T&A, waters. (1987). English for Specific purpose. Combridge: cup.

Johnson, P. (1982). “Effects on Reading Comprehension of Building Background Knowledge TESOL Quartely 16:4.

Karlin, R. (1981). Teaching Elementary Reading; Principles and Strategies.Hrvourt Brace and Jouanovich, Inc.

Kavale, K. (1979). “Selecting and Evaluating Reading Tests” In R. shreier (ed). Reading test and teachers: practical guide.

Klare, G.R. (1963). The Measurement of Readability; A Maslow state university press.

Laura, Q. (2011). Collaborate and Cooperate: Teacher education for integrating language and content instruction.

Lindsay, P.(2006). Learning and Teaching English. Oxford: Oxford University Press.

Madson H.S. (1983). Techniques in Testing. Oxford: Oxford University Press.

MC Donough, J. and Ch. Shaw (2003).Materials and Methods in ELT. Oxford: Oxford University Press.

Mei-Yun, Yue (1997). “Teaching Efficient EF2” IN karal, T. (ed) Teacher Development: Making the Right Moves. Washington, D.C: United States Information Agency.

Narayanaswamy, K.R. (1975). “ The Measurement of Reading Ability.” Journal of English Language Teaching, 29(2),

Nunan, D. (1988). Syllabus Design. Oxford: oxford university press.

Nuttal, C. (2000).Teaching Reading skills for in a Foregin Language. London. Heinemann Educational Books.

Nuttall, C. (1982).Teaching reading skills in a foreign language.Oxford; Heinemann publishers (Group) Ltd.

Nuttall, C. (1996).Teaching Reading Skills in aforein language.

Paris, S.G. (2005). Reinterpreting the development of Readng Skills.Reading Researche Quarterly, 40(2), 184-202

Prabu, M. H.(1987). Preparations for Educational Planning. Tehran: DonyayePajoohesh Publications. Emadzadeh, M.(2006). Economics of Education. Isfahan: ACECR

Richard, J.C and Schidt,R.(2002).Long man Dictionary of language teaching and applied linguistics

Richards, J. and Rodgers, T. (2001).Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C. (2001). Curriculum Development in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Robinson, P.(2011b). Second Language Task Complexity: Researching the Cognition Hypothesis of Language Learning and Performance. John Benjamins publishing company.

Schunk, D. H. (2003). Self-efficacy for reading and writing: Influence of modeling, goal setting, and self evaluation. Reading and Writing Quarterly, 19, 159-172.

Shanahan, T. (2006).Developing Fluency in the Content of Effective Literacy Instruction. In T. Rasinski, B. Camille and L. Kristin (Eds.) Fluency Instruction: Research Based Practices. Guilford Publication.

Sheng, H.J. (2000). A Cognitive Model for Teaching Reading Comprehension.The English Teaching Forum.Vo 38 Mum. 4pp 12-15.

Smith, F. (1985). Reading. Cambridge: Cambridge University Press.

Statman, S. (1981). The Advocation of a Systematic Theory: A Pedagogical Theory in the EFL Classroom Journal of English Language Teaching 35(3).

Stavans, A.(1993). Assessing EFL Reading Compherension: the Cause of System Ethiopian Learners, 21(4)

Stem, H.H. (1983). Fundamental Concept of Language Teaching.Oxford University.

Tag, C. and Wood Ward, E. (2011).Syllabus and Materials. University of Birmingham: CELS.

Tami Strang. (2012). The purposes of a syllabus. College Teaching, 50 (2),

Tufts, K. (2013). Designing and Developing Materials for Language Learning. Cambridge: Cambridge Universuty.

Ur. P. (1996).A course in Language Teaching practice and Theory. Cambridge: Cambridge University press.

Weir, C.J (1990).Understanding and Developing Language Tests. New York: Prentice Hall International Ltd.

Widdowson, H.(1990). Aspects of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Williams E. (1984). Reading in the Language class room.London McMillan publishers, Ltd.

Williams E. (1990). Reading in the Classroom. London: McMillan publishers, Ltd.

Yalden, J. (1983). The Communication Syllabus Evaluation, Design, and Implementation. Oxford: Peryamon Press.

## አባሪዎች

**አባሪ አንድ፡- በቴፒ ከተማ አስተዳደር ቴፒ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስረኛ ክፍል ተማሪዎችን አማርኛ ቋንቋ እያስተማሩ ላሉ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ፤**

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዓላማ "አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ በተዘጋጀው አስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸዉ ተጣጥሞሽ ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር አማርኛን በማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት የሚረዳን መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም እርስዎ የሚሰጡት ትክክለኛ መልስ ለጥናቱ ዓላማ ስኬት ትልቅ ሚና ስላለው መጠይቁን በመመለስ እንድትተባበሩኝ በትህትና እየጠየቅሁ ይህን መጠይቅ በመመለስ ስለተባበሩኝ በቅድሚያ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

**ክፍል አንድ፤**

**የትውውቅ ክፍል፤**

**መመሪያ፡- ቀጥሎ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ይስጡ፡፡**

ጾታ፡---------------- ዕድሜ፡-----------

የአገልግሎት ዘመን፡--------------

የትምህርት ደረጃ፡- ዲግሪ---------- ዲፕሎማ----------

የሚያስተምሩበት የትምህርት ዓይነት፡-----------------------

**ክፍል ሁለት፤**

በ2014 ዓ.ም. አዲስ የተዘጋጀውን የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን በተመለከተ የሚመለሱ ቃለ መጠይቆች፡-

**መመሪያ አንድ፡- እባክዎ መምህር ቀጥሎ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በጥሞና አዳምጠው ትክክለኛ ምላሽ ይስጡ፡፡**

1. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ ግቦችን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው?
2. በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ሁሉንም የመልመጃ ዓይነት አካትተው የያዙ ናቸው?
3. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የቀረቡት ተገቢ ገለጻ ከተሰጠ በኋላ ነው?
4. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ የመልመጃ ጥያቄዎች ሊይዟቸው የሚገባቸውን ባህሪያት የሚያሟሉ ናቸው?
5. በየክፍለ ጊዜው የተሸነሸኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ጋር የተጣጣሙ ናቸው? ካልሆነስ እንዴት እየተገበሩት ነው?
6. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በሁሉም ምዕራፎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የሚያስችሉ መልመጃዎች ተካተው ቀርበዋል? ጥያቄዎቹስ ከምንባቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ናቸው?
7. የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለመገንባት የቃላት ትምህርትን ያካተቱ መልመጃዎች በየምንባቡ ስር ተደራጅተዋል?
8. የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መልመጃዎች የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ መገምገም የሚያስችሉ ናቸው? ሁሉንም ተማሪዎች ታሳቢ ያደረጉ ናቸው?
9. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመርሀ ትምህርቱ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር የሚፈትሹ ናቸው?

10.በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር የተገናዘቡ ናቸው ብለው ያምናሉ? ካልሆነስ ምን አስተያየት ይሰጣሉ?


**መመሪያ ሁለት፡- የሚከተሉትን መጠይቆች በጥሞና አዳምጠው ትክክለኛ መልስ ይምረጡ፡፡**

1. የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ዝግጅትና የይዘት አቀራረብ ለክፍል ደረጃው ያላቸው ተስማሚነት ምን ያህል ነው?
   ሀ) በጣም ከፍተኛ ለ) ከፍተኛ ሐ) መካከለኛ መ) ዝቅተኛ
2. መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች መመሪያዎች ግልጽነት ምን ያህል ነው? ሀ) በጣም ከፍተኛ ለ) ከፍተኛ ሐ) መካከለኛ መ) ዝቅተኛ
3. የቀረቡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የማጠቃለል ችሎታ ለማሳደግ ምን ያህል ያስችላሉ? ሀ) በጣም ከፍተኛ ለ) ከፍተኛ ሐ) መካከለኛ መ) ዝቅተኛ
4. መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን የቃላት ሀብት እድገትን ለማሻሻል ምን ያህል ያተኮሩ ናቸው ብለው ያስባሉ? ሀ) በጣም ከፍተኛ ለ) ከፍተኛ ሐ) መካከለኛ መ) ዝቅተኛ

አባሪ ሁለት፡- Tufts (2013) "በወጉ የተዘጋጀ መርሀ ትምህርት በረካታ ጉዳዮችን አካቶ እንዲይዝ ይመከራል፡፡" ሲሉ የገለጹት መማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ስላለው ተጣጥሞሽ ለመለካት የተዘጋጁ መለኪያዎች፤

| ምዕራፍ | የመልመጃዎች ብዛት | ተገቢ የትምህርት ገለጻ በቅድሚያ ስለመደረጉ | | ተገቢ ዓላማ ስለመኖሩ | | ተማሪዎች የሚሰሩት ተግባራት ስለመቅረባቸው | | የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ስለመካተቱ | | የጊዜ መርሀ ግብር ተሸንሽኖ ስለመቅረቡ | | የምዘና ስልት ስለመካተቱ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የሚገናኝ | የማይገናኝ | የሚገናኝ | የማይገናኝ | የሚገናኝ | የማይገናኝ | የሚገናኝ | የማይገናኝ | የሚገናኝ | የማይገናኝ | የሚገናኝ | የማይገናኝ |
| አንድ | 3 | 3 | - | 3 | - | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| ሁለት | 3 | 3 | - | 3 | - | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| ሦስት | 4 | 4 | - | 4 | - | 4 | - | 4 | - | - | 4 | 4 | - |
| አራት | 3 | 3 | - | 3 | - | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| አምስት | 3 | 3 | - | - | 3 | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| ስድስት | 2 | 2 | - | 2 | - | 2 | - | 2 | - | - | 2 | 2 | - |
| ሰባት | 2 | 2 | - | - | 2 | 2 | - | 2 | - | - | 2 | 2 | - |
| ስምንት | 3 | 3 | - | 3 | - | 3 | - | 3 | - | - | 3 | 3 | - |
| ዘጠኝ | 2 | 2 | - | 2 | - | 2 | - | 2 | - | - | 2 | 2 | - |
| አስር | 2 | 2 | - | 2 | - | 2 | - | 2 | - | - | 2 | 2 | - |
| ድምር | 27 | 27 | - | 22 | 5 | 27 | - | 27 | - | - | 27 | 27 | - |

## አባሪ ሦስት፡- መምህራን ከመለሱት ቃለ መጠይቅ በናሙናነት የቀረበ መረጃ



ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በመምህራን የሚሞላ ቃለ መጠይቅ

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዓላማ "አዲስ በተዘጋጀው የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ ፍተሻ" በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር አማርኛን በማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት የሚረዳን መረጃ ለመሰብሰብ ነው። በመሆኑም እርስዎ የሚሰጡት ትክክለኛ መልስ ለጥናቱ ዓላማ ስኬት ትልቅ ሚና ስላለው ጥያቄዎችን በመመለስ እንድትተባበሩኝ በትህትና እየጠየቅሁ ይህን መጠይቅ በመመለስ ስለተባበሩኝ በቅድሚያ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

ክፍል አንድ፤

የትውውቅ ክፍል፤

መመሪያ፦ ቀጥሎ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ይስጡ።

ጾታ፦ ........

የአገልግሎት ዘመን፦ ....13....

የትምህርት ደረጃ፦ ዲግሪ ....✓.... ዲፕሎማ ........

የሚያስተምሩበት የትምህርት ዓይነት፦ ........

ክፍል ሁለት፤

በ2014 ዓ.ም. አዲስ የተዘጋጀውን የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን በተመለከተ የሚመለሱ ቃለ መጠይቆች፦

መመሪያ አንድ፦ እባክዎ መምህር ቀጥሎ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በጥሞና አዳምጠው ትክክለኛ ምላሽ ይስጡ።


1. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች በመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ ግቦችን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው? [illegible]
2. በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ሁሉንም የመልመጃ ዓይነት አካተው የያዙ ናቸው? [illegible]
3. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የቀረቡት ተገቢ ገለጻ ከተሰጠ በኋላ ነው? [illegible]
4. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች አንድን ምንባብ ተከትለው የሚመጡ የመልመጃ ጥያቄዎች ሲይዟቸው የሚገባቸውን ባህሪያት የሚያሟሉ ናቸው? [illegible]
5. በየክፍለ ጊዜው የተሰናሰሉ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ ጋር የተጣጣሙ ናቸው? ካልሆነስ እንዴት እየተገበሩት ነው? [illegible]
6. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በሁሉም ምዕራፎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የሚያስችሉ መልመጃዎች ተካተው ቀርበዋል? ጥያቄዎቹስ ከምንባቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ናቸው? [illegible]
7. የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለመገንባት የቃላት ትምህርትን ያካተቱ መልመጃዎች በምንባቡ ስር ተደራጅተዋል? [illegible]
8. የቀረቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መልመጃዎች የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ መገምገም የሚያስችሉ ናቸው? ሁሉንም ተማሪዎች ታሳቢ ያደረጉ ናቸው? [illegible]
9. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመርሀ ትምህርቱ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር የሚፈትሹ ናቸው? [illegible]
10. በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር የተገናኙ ናቸው ብለው ያምናሉ? ካልሆነስ ምን አስተያየት ይሰጣሉ? [illegible]

መመሪያ ሁለት፡- የሚከተሉትን መጠይቆች በጥሞና አዳምጠው ትክክለኛ መልስ ይምረጡ።

1. የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር የቀረቡት መልመጃዎች ዝግጅትና የይዘት አቀራረብ ለክፍል ደረጃው ያላቸው ተስማሚነት ምን ያህል ነው?
ሀ) በጣም ከፍተኛ ለ) ከፍተኛ ሐ) መካከለኛ መ) ዝቅተኛ
2. መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች መመሪያዎች ግልጽነት ምን ያህል ነው? ሀ) በጣም ከፍተኛ ለ) ከፍተኛ ሐ) መካከለኛ መ) ዝቅተኛ
3. የቀረቡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የተማሪዎችን የማጠቃለል ችሎታ ለማሳደግ የሚያስችሉ ናቸው? ሀ) አዎ ለ) አይደለም ሐ) ግልጽነት የላቸውም
4. መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን የቃላት ሀብት እድገትን ለማሻሻል ምን ያህል ያተኮሩ ናቸው ብለው ያስባሉ? ሀ) በጣም ከፍተኛ ለ) ከፍተኛ ሐ) መካከለኛ መ) ዝቅተኛ

እመሰግናለሁ!

**አባሪ አራት፡- አጥኚዋ በትምህርት ቤቱ ተገኝታ መረጃ ስለመሰብሰቧ ከትምህርት ቤቱ የተሰጣት ደብዳቤ**



ቁጥር: [illegible]/115

ቀን 13/07/2016

ለጂማ ዩንቨርሲቲ ሶ/ሳይ እና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢ/ያ ቋንቋዎች ና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትም/ት ክፍል

ጂማ

ጉዳዩ፡- ተማሪ ቆንጂት ሽደኖን ይመለከታል፤

በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው ከላይ በስም ተጠቃሽዋ ተማሪ ከዩንቨርሲቲው ባመጣችው ደብዳቤ መሰረት አዲስ በተዘጋጀው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መፅሀፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማስተማር የቀረቡ መልመጃዎችን ከመርሀ ትም/ቱ ጋር ተጣጥሞሽ ፍተሻ በትም/ት ቤታችን መረጃ በመሰብሰብ ቆይታ ያደረጉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

## የአጥኚዋ ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተጠቀሰው አጥኚ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የግል ስራዬ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸውንም ማጣቀሻዎች በትክክል ዋቢ ማድረጌን በፊርማዬ አረጋግጣለው፡፡

የአጥኚዋ ስም፡- ቆንጂት ሾደኖ ፊርማ ------------------